












መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ











## ማውጫ

1 መግቢያ ....................................................................................................... 1

2 የባለፉት 3 ዓመታት (2013-2015) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ...................................... 3

2.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት ............................................. 3
2.1.1 የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ ........................................... 3
2.1.2 የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ........................................................... 5
2.1.3 የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል ........................................ 6
2.1.4 ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር ............................................................ 7
2.2 የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ ................................................... 7
2.2.1 ቀጣይነት ያለው የህግና የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ ..................................................... 8
2.2.2 ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም ............................................................ 8
2.2.3 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል ............................ 9
2.2.4 የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ ............................................................... 10
2.2.5 የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ማረጋገጥ .......................................................... 11
2.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ................................................................. 11
2.3.1 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል ................................................ 12
2.3.2 የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል .............................................................. 13
2.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል ................................ 13
2.4 ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት ................................................................................ 14
2.4.1 የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል ........................................... 14
2.4.2 የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል ......................................... 14
2.5 ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ................................................................................... 15
2.5.1 የገቢ አፈጻጸም ግምገማ ................................................................................. 15
2.6 ባለፉት ሦስት ዓመታት የስትራቴጂክ ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት የአፈጻጸም ደረጃ አመላካቾች .......... 17

3 የገቢው ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች ......... 20

3.1 የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎች እና ዋና ዋና ተግባራት ................................ 20
3.2 የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ታሳቢዎች ........................................................................... 21
3.2.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ታሳቢዎች ......................................................................... 21
3.2.2 የታክስ ፖሊሲ ታሳቢዎች ................................................................................ 21
3.2.3 የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ............................................................... 21
3.3 ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ...................................................................................... 22

4 የመካከለኛ ዘመን (2016 — 2018) የልማት ዕቅድ ግቦች ፣ ዋና ዋና ተግባራትና ዒላማዎች ................. 24

4.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት ............................................. 24
4.1.1 የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ ........................................... 24
4.1.2 የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ........................................................... 24
4.1.3 የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል ........................................ 24
4.1.4 ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል .............................................................. 25
4.2 የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ ................................................... 25
4.2.1 ቀጣይነት ያለው የህግና የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ ..................................................... 25

4.2.2 ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም ........ 26
4.2.3 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል ........ 26
4.2.4 የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ ........ 27
4.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ........ 28
4.3.1 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል ........ 28
4.3.2 የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል ........ 29
4.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል ........ 29
4.4 ስትራቴጂ አጋርነት ልህቀት ........ 30
4.4.1 የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል ........ 30
4.4.2 የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነት ........ 30
4.5 ዘላቂ ገቢ ዕድገትን ማረጋገጥ ........ 31
4.5.1 ዘላቂ ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ........ 31
4.6 2016 — 2018 የተቀመጡ ግቦች ........ 32
4.6.1 ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ........ 32
4.6.2 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ........ 32
4.6.3 የታክስና ጉምሩክ አሰራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ ........ 33
4.6.4 ስትራቲጂክ አጋርነት ልህቀት ........ 34
4.6.5 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ........ 35
5 የመካከለኛ ዘመን ኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች ........ 36
5.1 የመካከለኛ ዘመን የኢንቨስትመንት ፍላጎት ........ 36
5.2 የዝርዝር ዓመታዊ የኢንቨስትመንት ዒላማዎች በፕሮጀክቶች ........ 40
6 ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 47
7 የክትትልና ግምገማ አሠራርና ሥርዓት ........ 49
7.1 የክትትል ሥርዓት ........ 49
7.2 የግምገማ ሥርዓት ........ 50
7.3 ለክትትልና ግምገማው የሚያስፈልገው አደረጃጀትና የሰው ኃይል ........ 50
7.4 ክትትልና ግምገማውን በቴክኖሎጂና አሠራር ሥርዓት ማስደገፍ ........ 51
7.5 የግብረ - መልስ ሥርዓት ........ 51
8 እዝሎች ........ 53

# 1 መግቢያ

የሀገሪቷን የአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ መንግስት የነደፋቸውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕቅዶች ፋይናንስ ማድረግ የሚያስችል ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ ሁሉን ዓቀፍ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ውጤታማ ተግባራቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ የዕቅድ ውጤታማ አፈጻጸም የሚወሰነው ነባራዊ የሀብት አቅምና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ የረጅም ጊዜ ግቦችን ወደ አጭርና መካከለኛ ዘመን ዕቅድ በመመንዘር ለማሳካት የሚያስፈልጉ የማስፈጸሚያ ፕረግራሞችና ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል በማስያዝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ፣ ባለፉት ሦስት የአስር ዓመቱ ዕቅድ ትግበራ ዓመታት በርካታ አበረታች ስኬቶች የተመዘገቡ ቢሆንም፣ ሀገራችንን ባጋጠሟት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎች ምክንያት፣ የልማት ፕሮጀክቶችና ኢንቨስትመንቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና ወጪ እንዳይጠናቀቁ የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል፡፡ ከዚህም በመነሳት ያለፉትን ሦስት ዓመታት (2013- 2015) የአስር ዓመቱ የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ቀጣይ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ መንግስት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የገቢው ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ማገገሚያ ለማስቀጠል፣ የተፋጠነ ዕድገት ለመደገፍ፣ የኢንቨስትመንት ውጤማነትን ለማረጋገጥና ማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት በሚደረገው ጥረት አካል ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

የገቢው ዘርፍ የተሰጡትን ስልጣንና ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችል ለሀገራዊ ዕድገት እና ሁለንተናዊ ልማት አጋዥ የሆነ የአስር ዓመታት (2013-2022) የልማት መሪ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የዘርፉን የረዥም ጊዜ የልማት ግቦችን ወደ አጭርና መካከለኛ ዘመን ዕቅድ በመተርጎም ግቦቹን ለማሳካት የሚያስፈልጉ የማስፈጸሚያ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል በማስያዝ ማቀድ በማስፈለጉ ያለፉትን ሶስት ዓመታት (2013-2015) የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም እና የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ግምገማ በማካሄድ የተከለሰ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማትና የኢንቨስትመንት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ይደረስበታል ተብሎ ከተተነበየው 348 ቢሊዮን ብር ገቢ በመካከለኛ ዕቅድ ዘመኑ ማብቂያ (2018) ወደ 766.7 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

የተዘጋጀው የመካከለኛ ዘመን የልማትና የኢንቨስትመንት ዕቅድ ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተቀዳና የተጣጣመ ሆኖ የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን በ2022 ዘመናዊ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በቀረጥና ታክስ ገቢ ተሸፍኖ የማየት ርዕይ ላይ ለመድረስ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም የገቢው ዘርፍ ወደዚሁ ርዕይ የሚያደርሰውን ተልዕኮ ማለትም ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የታክስና ጉምሩክ አገልግሎት በመስጠት፣ ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፣ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን በመከላከልና በመቆጣጠር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ ነው፡፡ ይህንኑ ተልዕኮ ለማሳካት አገልጋይነት፣ መስጠት፣ ሙያዊ ብቃት፣ ታማኝነት እና በቡድን የመስራት እሴቶችን በመላበስ ይሰራል፡፡

የመካከለኛው ዘመን (2016-2018) ዕቅድ ሲቀረጽ አምስት ስትራቴጂክ ግቦች የተለዩ ሲሆን እነዚህም ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት፣ የታክስና የጉምሩክ አሰራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ፣የታክስ እና የጉምሩክ ህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ፣ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት ማረጋገጥ እና ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማምጣት ናቸው፡፡ የተቀረጹትን ስትራቴጂክ ግቦችን ማሳካት የሚያስችሉ ዋና ዋና ተግባራት እና ስኬት ለማረጋገጥ የሚያግዙ ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን በመቅረጽ የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስችሉ ዓመታዊ ዒላማዎች ተቀምጠዋል፡፡

የዕቅድ ሰነዱ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት የባለፉት ሶስት ዓመታት (2013-2015) የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ጉዞ አፈጻጸም ግምገማ፣ በክፍል ሶስት የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች፣ በክፍል አራት የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራትና ዒላማዎች፣ በክፍል አምስት የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች፣ በክፍል ስድስት የአደጋ ስጋት ግምገማ ስጋቶች ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች እና በመጨረሻው ክፍል የክትትልና ግምገማ አሰራርና ስርዓትን በማካተት የስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነዱ በሰባት ክፍሎች ተደራጅቶ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

# 2 የባለፉት 3 ዓመታት (2013-2015) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

## 2.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት

### 2.1.1 የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ

የገቢው ዘርፍ በስትራቴጅክ እቅዱ ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት እንዲቻል ቁልፍ ሚና ያለውን የሰው ኃይል ከማሟላት፣ ከማብቃት፣ የስራ ቦታዎችን ለተገልጋዩና ለሰራተኛ ምቹ ከማድረግ እንዲሁም የስራ ተነሳሽነትን የሚጨምሩ የሰራተኛ እውቅናና ማበረታቻ ስርዓቶችን ከመዘርጋትና ከመተግበር አኳያ ባለፉት ሶስት ዓመታት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል። በዚህም ከሰው ኃይል ሙሌት አንጻር 981 አዳዲስ ሰራተኞችን የጾታ ስብጥርን ማዕከል ባደረገ አግባብ ትኩረት ሰጥቶ የሰው ኃይል ሙሌት በማከናወን የሰው ኃይል ቁጥሩ በ2013 ዓ.ም ከነበረው 12,527 በ2015 ዓ.ም ወደ 13,508 ማድረስ ተችሏል። የሰው ኃይሉ በእቅዱ መሰረት ባይሟላም ያለውን የሰው ኃይል ውጤታማ በሆነ አግባብ ስምሪት በመስጠት የታክስ ህግ ተገዥነትን በማጠናከር የባለፉት ሶስት ዓመታት የገቢ ዕቅድ አፈጻጸም እንዲሻሻል ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል።

ከሰው ሀብት ፍላጎት ጋር በተያያዘ ከታች ለማሳየት እንደተሞከረው በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ መድረስ ባለመቻሉ በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን የስትራቴጂክ ዕቅድ ጊዜ ውስጥ ተቋሙ ተግባራዊ የሚያደርጋቸውን ቴክኖሎጂዎች እና የአሠራር ስርዓት ማሻሻያዎች እንዲሁም የገቢ አሰባሰብ ማሳካት በሚያስችል አግባብ የሰው ሀብት ፍላጎት ዕቅዱን መከለስ ያስፈልጋል።

**ምስል 1፡ የሰው ሀብት ሙሌት ከስትራቴጂክ ዕቅድ አኳያ**




በተቋሙ ያለውን የሰው ኃይል ተነሳሽነቱን በማሳደግ እና ማቆየት እንዲቻል አቅም በፈቀደ መልኩ የስራተኛ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ማሻሻል ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። በዚህም ለሰራተኛው የሰርቪስ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ማቅረብ፣ የስራና አደጋ መከላከያ እንዲሁም የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲቀርቡ መደረጉ፣ በተወሰነ መልኩ የካፊቴሪያ አገልግሎት እንዲያገኝ መደረጉ፣ በ2014 ዓ.ም የተቋሙን የገቢ አፈጻጸም መሰረት በማድረግ የደመወዝ ሁለት እርከን ጭማሪ መደረጉ፣ የደረጃ ዕድገት፣ የሰራተኛውን ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የዝውውር እንዲሁም አነስተኛ ደመወዝ ለሚከፈላቸው ሰራተኞች በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ሰራተኛውን ለማቆየትና ለማበረታታት በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል።

ይሁን እንጂ የተቋሙ ደመወዝ እስኬል ከስድስት ዓመት በፊት በ2009 ዓ. ም ከተደረገለት ማሻሻያ በስተቀር ክለሳ ያልተደረገበት በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር ሰራተኛው ላይ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ተቋሙን በሰው ኃይል ገበያው ውስጥ ተወዳዳሪ ከማድረግ አንጻር በእጅጉ አናሳ መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን በዚህም ባለፉት ሶስት ዓመታት 1408 ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በራሳቸው ፈቃድ

ተቋሙን ለቀዋል::በመሆኑም ተቋሙ ሰራተኛውን በማቆየት ተነሳሽነት ፈጥሮ ቀጣይ ዕቅዱን ማሳካት እንዲችል የወቅቱን የሰው ኃይል ገበያ መሰረት በማድረግ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል:: የተቋሙ ስራ በባህሪው ከፍተኛ ዕውቀት፣ ስነ-ምግባርና እስከ ህይወት መስዋዕትነት ድረስ የሚጠይቅ ሲሆን በተለይ ኮንትሮባንድን በመከላከል ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞቻችን የአካልም ሆነ የህይወት መስዋዕትነት በሚያጋጥማቸው ወቅት በተቋሙ የሚደረግ ድጋፍ እምብዛም በመሆኑ ሰራተኞቹም ሆነ ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ችግር የሚጋለጡ ሲሆን ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የመድህንና የህክምና ሽፋን ሊመቻች ይገባል::

የሰው ኃይል ምርታማነትን ለማሳደግ የታክስ እና ጉምሩክ ስልጠና ማዕከል በማደራጀት የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል:: በዚሁም በተለያዩ ርዕሶች ላይ በ2013 ዓ.ም ለ5,233፣ በ2014 ዓ.ም ለ3,453 እና በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ለ3,383 ሰራተኞች በስራ ላይ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ተደርጓል:: በረጅም ጊዜ ስልጠና በሶስቱ ዓመታት በሁለተኛ ድግሪ 187 እና በዶክትሬት ድግሪ 10 በድምሩ ለ197 ሰራተኞች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለ19 ሰራተኞች የውጪ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል::

**ምስል 2፡ የሰራተኛ ምርታማነት አፈጻጸም**




ከሰው ሀብት አቅም ግንባታ አንጻር ባለፉት ሶስት ዓመታት በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ተቋሙ በራሱ የስልጠና ማዕከል ስልጠና መስጠት ባለመጀመሩ ካለው የሰው ኃይል ስፋት አንጻር ስልጠናውን በሚፈለገው ደረጃ ማከናወን አለመቻሉ፣ የሰልጣኞች ልየታ ከተፈላጊ ችሎታ መስፈርት (Competency Framework) ጋር አቀናጅቶ አለመፈጸም፣ የተሰጡ ስልጠናዎች ውጤታማነትን ከመገምገም እና ስልጠናዎች የሚሰጡበትን አግባብ ከማስፋት አንጻር ክፍተቶች ታይተዋል:: በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖር በመስራት ልምድ ለመቅሰም የሚያስችሉ የስልጠና ዕድሎችን ከማፈላለግ አንጻርም የተደራጀ አሰራር ያልተዘረጋ በመሆኑ በቀጣይ በሚዘጋጀው የሰው ሀብት ስትራቴጂ ውስጥ ተካተው በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል::

ከሠራተኛ ማበረታቻ፣ የማትጊያ እና ማቆያ ስርዓት ጋር በተያያዘ በየዓመቱ የሰራተኞች ዕውቅና እና ማበረታቻ ፕሮግራሞች ላይ በአፈጻጸማቸው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሠራተኞችንና አመራሮች እንዲሁም የስራ ክፍሎችን ለማበረታታት ጥረቶች ተደርገዋል:: በዚሁም በ2013 (የ2012 አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ) 185 አመራሮችና ሰራተኞች፣ ለ29 የስራ ክፍሎች እና 8 ልዩ ተሸላሚዎች እና በ2014 (የ2013 አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ) ለ217 አመራሮችና ፈጻሚዎች፣ 30 የስራ ክፍሎች እንዲሁም 5 ልዩ ተሸላሚዎች ዕውቅና እንዲያገኙ ተደርጓል::

ከሰራተኛ ዕውቅናና ማበረታቻ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በመመሪያ ያልተደገፈ መሆኑ፣ የዕውቅናና ሽልማት ስራዎችን ከውጤትና ከትክክለኛ መረጃ ጋር ከማስተሳሰርና በግልጸኝነት ከመተግበር አንጻር ክፍተት የነበረበት

በመሆኑ በሰራተኞች ዘንድ ቅሬታ የፈጠረ ስለመሆኑ የሰራተኛ ዕርካታ ዳሰሳ ጥናት ያመላክታል፡፡ በቀጣይ ይህን ችግር በመፍታት የሽልማት እና ዕውቅና ስርዓቱ ግልጽ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ በመመሪያ ተደግፎ ሊፈጸም ይገባዋል፡፡

በአጠቃላይ በታክስና በጉምሩክ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎችን ዕርካታ በማሳደግ በተቋሙ ውስጥ ለማቆየት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ባለፉት ሶስት ዓመታት በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተያዙ የሰራተኛውን ዕርካታ ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራት በተሟላ ሁኔታ ባለመፈጸማቸው የሰራተኛ ዕርካታ ከዕቅዱ አንጻር እየቀነሰ እንደመጣ መረጃው ያመለክታል፡፡ በዚሁም የሰራተኛ ዕርካታ በ2013 በጀት ዓመት ከነበረበት 54.4 በመቶ በ2014 ወደ 48.3 በመቶ ቀንሷል፡፡

በ10 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ከሰው ሀብት ስራ አመራር አንጻር ስራዎችን ለመለካት የተቀመጡ መለኪያዎች የምርታማነት እና የወጪ አመልካቾች ብቻ በመሆናቸው ስራውን ሙሉ በሙሉ ለመመዘን ያላስቻለ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም የሰው ሀብት ስራዎችን ጥቅል በሆነ መልኩ ለመመዘን እንዲቻል ቀድሞ ከተለዩ መለኪያዎች በተጨማሪ የሰው ሀብት አስተዳደር ውጤታማነት መለኪያ በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በዚህም መለኪያ የሰው ሀብት ስራዎችን ማለትም የሰራተኛ ቅጥር፣ ዝውውር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ትምህርትና ስልጠና፣ ምዘና፣ ሽልማት እንዲሁም ስንብት ስራዎችን የአፈጻጸም ውጤታማነት ለመለካት ያስችላል፡፡

በመካከለኛው ዕቅድ ዘመኑ የተቋሙን ርዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሰው ኃይሉ ያለውን ቁልፍ ሚና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መብቱ የተከበረ፣ ነጻ ሆኖ የሚያገለግል፣ ጥቅሞቹ የተከበሩለት፣ አምራች የሆነ እና በስነ-ምግባር የታነጸ ሰራተኛ ለመፍጠር የሰራተኛውን ዕርካታ በማረጋገጥ ምርታማነቱን የሚያሳድጉ ስትራቴጂክ ስራዎችን ለይቶ በከፍተኛ ትኩረት ማከናወን ይጠበቃል፡፡

## 2.1.2 የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ

ተቋሙ የተመደበለትን የመደበኛና የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ባለፉት ሶስት ዓመታት በዕቅድ የተያዙ ግቦችን በውጤታማነት አጠናቋል፡፡ በዚህም ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ግዥ ፈጽሞ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት የገቢ አሰባሰቡን በአግባቡ የመደገፍ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም ተቋሙ ከዚህ ቀደም ከኦዲት ግኝት ማስተካከያ ጋር በተያያዘ በፌደራል ዋናው ኦዲተር በተደጋጋሚ ሲቀርብበት የነበረ ቢሆንም በየጊዜው በተሰሩ የክትትልና የግኝት ማስተካከያ ስራዎች የተነሳ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ኦዲት አስተያየት ከተወሰኑ የአሰራር ጥሰቶች በስተቀር የወጪ፣ የበጀት እና የሂሳብ ምዝገባ ሥርዓቱ የመንግስት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትሎ የተሰራ መሆኑን አስተያየት እንዲሰጥ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በቀጣይ ስትራቴጂ ዘመንም ይህንኑ በማስቀጠል እና የተሻለ ውጤት በማምጣት ከግኝት የጸዳ ተቋም ለመፍጠር የሚሰራ ይሆናል፡፡




ከላይ የተጠቀሱት ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ግዥዎችን በወቅቱ በጥራት ከመፈጸም፣ ለስራ አስፈላጊ የሆኑ በቂ ተሽከርካሪዎችን ከማቅረብ እና ከፕሮጀክቶች በጀት አጠቃቀም አንጻር ውስንነት ይታያል፡፡

ለሰራተኞች ሰርቪስ ኪራይ በየዓመቱ በአማካይ ከ257 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚደረግ ሲሆን፣ የጉምሩክ ዋና መ/ቤትን ጨምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ ታክስ እና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ በየዓመቱ ለቢሮና መጋዘን ኪራይ በአማካይ 536 ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ የሚከፈል በመሆኑና ይህም ከፍተኛ ሀብት በመሆኑ ተቋሙ የራሱ የሆነ ቢሮ መገንባት እና ለሰራተኛ ሰርቪስ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎችን መግዛት በትኩረት ሊፈጸም ይገባዋል፡፡

የፕሮጀክቶች አፈጻጸሙ አነስተኛ በመሆኑ የካፒታል በጀት አጠቃቀሙ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለ ሲሆን ለዚህም በዋነኝነት የሚጠቀሱት ምክንያቶች ፕሮጀክቶችን ቅድመ ሁኔታዎችን ሳይጨርሱ መጀመር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የጸጥታ ችግር የተነሳ የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚ ጊዜ እንዲራዘም መደረጉ፣ የቴክኖሎጂ ግዥዎች መጓተት፣ ከዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ ወቅታዊ የግብዓት አቅርቦት አለመኖር፣ የስራ ተቋራጮች የአቅም ማነስ እንዲሁም የተቋሙ የማስፈጸም አቅም ውስን መሆን የተወሰኑ ተጠቃሽ ምክንያቶች መሆናቸው ታይቷል፡፡ በመሆኑም ችግሮቹን በመፍታት በቀጣይ በፕሮጀክቶች አስተዳደር ስራዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራ ይገባል፡፡

### 2.1.3 የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል

የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሴቶችና በወጣቶች፣ በህጻናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በኤች.አይ. ቪ. ኤድስ፣ በጤና እና አካባቢ ጥበቃ ስራዎች፣ በስርዓተ ጾታ ዙሪያ የወጡ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ አዎንታዊ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የሴቶች ተሳትፎን ከማረጋገጥ አንጻር በቅጥር የሴቶችና ወንዶችን ቁጥር በማመጣጠን የሴት ሰራተኞችን ቁጥር ለማሳደግ በተሰራው ስራ የሴት ሰራተኞች ድርሻን 49 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት የሴት ሰራተኞችን በልዩ ሁኔታ በማብቃት እና ሴት ተኮር የሆኑ ተጨማሪ ስራዎችን በመስራት በስትራቴጂክ ዕቅዱ የሴት ሰራተኞች አመራር ድርሻን 50 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሎ የነበረ ቢሆንም አፈጻጸሙ ሲገመገም በ2015 በጀት ዓመት ማድረስ የተቻለው 32 በመቶ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተቋሙ በቀጣይ በሚተገበረው የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ለየት ያለ ስትራቴጂ በመንደፍና የሴት ሰራተኞችን በማብቃት በሽፋኑ ላይ የተመዘገበውን ውጤት እንደ ምርጥ ተመክሮ በመውሰድ ሴቶችን ወደ አመራር እርከን ከማምጣት አኳያ ከፍተኛ ስራዎችን መስራት ይገባዋል፡፡

ከማህበራዊ አገልግሎት አንጻር በኤች.አይ. ቪ. ለተጎዱ ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ በማድረግ፣ በአረንጓዴ አሻራ እና ገበታ ለሀገር መርሃ ግብር ላይ ጠንካራ ተሳትፎ በማድረግ እንዲሁም በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ የህብረሰተብ ክፍሎች ፈጥኖ በመድረስ ተቋሙ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን በሶስቱ

የዕቅድ ትግበራ ዓመታት “የህዝብን ሀብት ለህዝብ” እና “ለወገን ደራሽ ወገን ነው” በሚባሉ ሁለት መርህዎች መሰረት ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት በገንዘብና በዓይነት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲደርስ አድርጓል። በዚህም ከተለያዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ከህብረተሰብ ተወካዮች እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት አበረታች ዕውቅናዎችን ያገኘ ሲሆን ይህም ተቋሙ ገቢ ከመሰብሰብ ኃላፊነቱ በተጨማሪ ይሄንን በጎ ተግባር ማከናወን በመቻሉ ለሌሎች ተቋማት ተምሳሌት መሆን ከመቻሉም በላይ የተቋሙ ገጽታ እንዲሻሻል አድርጓል።

**ምስል 3፡ በተቋሙ በቦረና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የተደረገ ድጋፍ**



ይሁንና ባለፉት ሶስት ዓመታት ከላይ የተገለጹት አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ሴቶችን ወደ አመራር ከማምጣት እና ለአካል ጉዳተኞች በተሟላ መልኩ ምቹ የስራ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር ውስንነቶች የተስተዋሉ በመሆኑ በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ውስጥ የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና የማህበራዊ ኃላፊነት ስራዎች ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

### 2.1.4 ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር

ባለፉት ሶስት ዓመታት ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸም ለማሻሻል እንዲያስችል ስጋቶችን የመለየት፣ የመተንተን እና የስጋት ስትራቴጂ የመቅረጽ፣ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን የመፈተሽና የማስተካከል እና የስነ-ምግባር ችግር በሚታይባቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ላይ ባለው ህጋዊ አሰራር መሠረት እርምጃ በመውሰድ ተቋማዊ ጤንነትን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። ይሁንና የተቀረጸውን ስትራቴጂ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ከማድረግና የስነ- ምግባር ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ እንዲስተካከሉ ከማድረግ አንጻር ውስንነቶች ተስተውሏል። በመሆኑም በቀጣይ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር የስራ ባህርይ እና ሁኔታ ያለውን የስጋት ተጋላጭነት ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የተቋማዊ የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ ስጋትን በመቀነስ የገቢ ሴክተሩን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስራ መስራት ያስፈልጋል።

## 2.2 የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ

በዚህ ስትራቴጂክ ግብ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ከመገንባት አንጻር የህግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻልን፣ አዳዲስ አሰራሮችን መቅረጽን እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ

በማስደገፍ የላቀ አገልግሎት መስጠትን፣ ህግን ማስከበር እና የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግን የሚያካትት ሲሆን የባለፉት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ከዚህ በታች ባለው አግባብ ቀርቧል።

### 2.2.1 ቀጣይነት ያለው የህግና የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ

የታክስና ጉምሩክ የህግና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች በማከናወን የአገልግሎት አሰጣጡ፣ የቁጥጥር ስርዓቱ እና የገቢ አሰባሰብ ስራውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስችሏል። በዚሁ መሠረት ባለፉት ሶስት የስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመታት አፈጻጸም ወቅት ከተከናወኑ ዋና ዋና የህግና አሰራር ማሻሻያዎች መካከል የጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ፣ የጉምሩክ ደንብ እና 23 የተለያዩ መመሪያዎች በማጽደቅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል።

አሰራር ከመቅረጽ አንጻር ያለጥሬ ገንዘብ ክፍያ ዕቃዎች በባንክ ዋስትና የሚለቀቁበት /Deferred Payment/ አሰራር፣ ዕቃ ሳይደርስ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም (Pre-arrival Clearance Procedures) አሰራር፣ የአስገዳጅ የታሪፍ መረጃ አሰጣጥ (Advance Rulling) ስርዓት፣ በጥቅልና በክፍልፋይ /Consolidated and Deconsolidated/ የሚመጡ ጭነቶችን የማስተናገጃ ስርዓት፣ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ማስፈጸሚያ ኮድ (Customs Procedure Code) አሰራር፣ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ አጠቃቀም ስርዓት፣ በዕቃ አወጣጥ ስርዓት ላይ ዕሴት የማይጨምሩ ሰነዶች የሚቀነስ አሰራር እና የመሳሰሉትን ተግባራዊ በማድረግ ለንግድ ስራ አመቺነት (Ease of Doing Bussines) ከማረጋገጥ እና ሎጂስቲክስን በማፍጠን እንደ ሀገር ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል።

ግብር ከፋዮች በአካል ወደ ገቢ ተቋማት መምጣት ሳያስፈልጋቸው ግብራቸውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አሳውቀው ክፍያ መፈጸም እንዲችሉ የኢ-ታክስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል። በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ታክሳቸውን በኤሌክትሮኒክስ የሚያሳውቁ (E-filing) ግብር ከፋዮች ሽፋንንን በ2015 ዓ.ም 100 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ 82 በመቶ ተከናውኗል። በሌላ መልኩም በ2012 መጨረሻ ከነበረው 20 በመቶ ሽፋን በ2015 ወደ 82 በመቶ ማድረስ መቻሉ የዕቅድ ዘመኑ ስኬት ነው። የኢ-ክፍያ ስርዓቱን ለማሳደግም በኢ-ክፍያ (E-payment) የሚሳተፉ ባንኮችን ቁጥር ከአንድ ባንክ ወደ 17 ባንኮች በማሳደግ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። በ-ኢ.ታክስ የከፈሉ ግብር ከፋዮች ሽፋንም በ2015 በጀት ዓመት 60 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሎ የነበረ ቢሆንም ማሳካት የተቻለው 39 በመቶ ነው። እንደ አጠቃላይ በተቋሙ የኢ-ታክስ ስራዎች መስፋፋትና ለገቢ አሰባሰቡ ማነቆ የሆኑ አሰራሮችን በመፍታትና የተገልጋዩን ጊዜና የታክስ ባለስልጣኑንም የአገልግሎት ጫና በመቀነስ ረገድ ጉልህ ድርሻ አበርክተዋል።

ይሁንና የሚሻሻሉና በአዲስ መልክ የሚቀረጹ ህጎችና አሰራሮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያመጡትን ውጤት በተከታተይ በዳሰሳ ጥናት ከመለየት፣ የውስጥና የውጭ ፈጻሚ አካላትን አቅም ከመገንባት እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ከማድረግ አንጻር የኢ-ክፍያ ሽፋኑ በሚፈለገው ደረጃ ያልሰፋ መሆኑና የግብር ከፋዩም ግንዛቤ አለማደግ ውስንነቶች ተስተውለዋል።

በቀጣይ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደሩን ለማዘመን ተከታታይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ማድረግ ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡና በገቢ አሰባሰቡ ላይ በተጨባጭ የሚታዩ ችግሮችን በጥናት በመለየት ዓለም ዓቀፍ ልምድን በማካተት የላቀ አሰራር በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል የገቢ አሰባሰቡን እና የግብር ከፋዩን የህግ ተገዥነት ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል።

### 2.2.2 ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም

የፌደራል ታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ከማጣጣምና የክልል ገቢ ተቋማትን ከመደገፍ አንጻር የቴክኖሎጂ እና የቁሳቁስ ድጋፍ፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲሁም የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር የማጣጣም ስራዎች ተሰርተዋል። ባለፉት 3 ዓመታት 1,732 የክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ባለሙያዎች በታክስ ህጎችና በተለያዩ

ርዕሶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክልል የገቢ ሰብሳቢና የፋይናንስ ዘርፍ ተቋማት ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርዓት (የምክክር መድረኮችን) በማካሄድ የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር አፈጻጸሞችን በጋራ በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም በክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮች እና በፌደራል ደረጃ ከምን ጊዜውም በተሻለ በገቢ ትልልፍና ድጋፍ ላይ ተዓማኒነት ያለው ግንኙነት እንዲፈጠር አስተዋጽዎ አድርጓል፡፡

ይሁን እንጂ የታክስ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎች በሚጠበቀው ደረጃ ከማጣጣም አንጻር ቀሪ ስራዎች መኖራቸው፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚደረገው የቴክኖሎጂ ድጋፍ ውስንነት መኖሩ በእጥረት የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የጋራ የምክክር መድረኮችን በማጠናከር የሚጠበቁ ድጋፎችን በማድረግ የክልሎችን አቅም መገንባትና የታክስ ስርዓቱን በሚፈለገው ደረጃ የተጣጣመ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.2.3 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል

የታክስና ጉምሩክ መረጃ ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለገቢ አሰባሰብ፣ ለህግ ተገዥነት ሥራዎች፣ ለተለያዩ የጥናት ስራዎችና ለፖሊሲ አውጭዎች ቁልፍ ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት ተቋሙ በዘረጋቸው የተለያዩ የመረጃ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ በማዋል ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ባለፉት ሦስት ዓመታት የሽያጭና ግዥ መረጃዎች 22,280,062 እና 109,472 የፊዚካል መረጃ እንዲሁም የግብር ከፋይ የታክስ ማስታወቂያ መረጃዎች ለታክስ ውሳኔ ጥቅም ላይ በማዋል የገቢ አሰባሰቡ ውጤታማ ማድረግ ተችላል፡፡ የጉምሩክ እና ሀገር ውስጥ ታክስ ድህረ ገጾችን የማሻሻል ስራዎች በመስራት ግብር ከፋዩ ወቅታዊ መረጃን በድህረ ገጽ ማግኘት በመቻሉ ግንዛቤው እንዲጨምርና ለታክስ ህግ ተገዥነት መጨመር አስተዋጽዎ አበርክቷል፡፡

በጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ስርዓት የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች መረጃ፣ በትራንዚት ጉምሩክ ስነ-ስርዓት ወደ ሀገር የሚገቡና የሚወጡ ጭነቶች መረጃ፣ እንዲሁም በመጋዘን ጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተከማችቶ የሚገኙ ዕቃዎች መረጃ በአግባቡ በማደራጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ አስችሏል፡፡ በተጨማሪ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ዘመን ከ30 ሚሊዮን በላይ የዕቃዎች ዋጋ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ወቅታዊ አድርጎ በማሰራጨት የቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ስርዓቱን የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል፡፡

በሌላ መልኩ የአስመጪዎችን፣ የላኪዎችን፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎችንና የዕቃዎችን 285,526 መረጃዎችን ባላቸው የስጋት ደረጃ መሠረት ወቅታዊ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ እና የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ስራዎችን በስጋት ስራ አመራር እንዲመሩ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከሶስተኛ ወገንና ከሲስተም የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን የኮንትሮባንድና ንግድ ማጭበርበርን የመከላከል ስራው የተጠናከረ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይሁንና በተለያየ አግባብ የሚደራጁ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ ከመተንተን አንጻር የሚታዩ ክፍተቶች፣ አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ እጥረት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የገቢ እና ወጪ ጭነቶች ከማስታረቅ አንጻር እንዲሁም በጉምሩክና በሀገር ውስጥ ታክስ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩ ከሚስተዋሉ ውስንነቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን የታክስና የጉምሩክ የመረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን አስተማማኝ የመረጃ ምንጮችን በማስፋት፣ የትልልቅ መረጃዎች ትንተና አቅምን በማሳደግ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ በማጠናከር የአገልግሎት አሰጣጡን፣ የገቢ አሰባሰቡን እና የህግ ተገዥነት ስራውን ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.2.4 የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ

በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ታምኖበት በአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ ከዚህ አኳያ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል:: በዚሁ መሠረት የወጪና ገቢ ንግድ ለማሳለጥና የወረቀት አልባ አገልግሎት መተግበርና ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ዕውን ከማድረግ አንጻር የIT Strategy ጸድቆ መተግበሩ፣ የጉምሩክ ስራ አመራር አስተዳደር ስርዓት (eCMS) ተግባራዊ መደረጉ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ በአንድ ማዕከል ለማድረግ ያስቻለ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት (eSW) በስራ ላይ መዋሉ፣ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመወሰን የሚያስችል የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS_G2) በስራ ላይ መዋሉ፣ በትራንዚት ላይ ያሉ ዕቃዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ የዕቃ መፈተሻ ስካኒንግ ማሽን (Cargo Scanning Machine) ስራ ላይ መዋሉ በጥንካሬ ሊነሱ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ስራዎች አፈጻጸም ናቸው::

በተጨማሪነት የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማቀላጠፍ በስራ ላይ ውሎ የነበረውን የተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) የኢ-ማሳወቅና የኢ-ክፍያ ስርዓቶችን በማቀናጀትና በማስፋት አዳዲስ የወጡ እንደ ኤክሳይዝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅና ደንቦችን መሰረት በማድረግ የቴክኖሎጂ ማሻሻያ መደረጉ፣ በስራ ላይ ለታክስ አወሳሰን ግብዓት የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃ መሰብሰቢያ(TASS) ማሻሻያ መደረጉ፣ በስራ ላይ የነበረውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስርዓት ከቀድሞው በተሻለ መልኩ መረጃ እነዲቀበል የማሻሻያ ስራዎች መሰራታቸው፣ የግብር ከፋዮች አጠቃላይ መረጃ በማሰባሰብ ማለትም የጉምሩክና የሶስተኛ ወገን መረጃ በያዘ መልኩ ከአንድ ቦታ ለስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚያደርግ የዳታ ዌርሃውስ ለምቶ በስራ ላይ እንዲውል መደረጉ፣ የክልል ገቢ ትልልፍ ስርዓት ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ መደረጉ፣ ግብር ከፋዮች በወረቀት አልባ ከየትኛውም ቦታ ሆነው ግብርና ታክሳቸውን የሚያሳውቁበት (E-Filing) ከበፊቱ በተሻለ የሲስተም ማሻሻያ ተደርጎለት የክልል  ግብር ከፋዮችን ጨምሮ በርካታ ግብር ከፋዮችን ማስተናገድ እንዲችል የማሻሻያ ስራ መሰራቱ፣ የካሽ አልባ የግብር ክፍያ ሥርዓት (E-Payment) የነበሩበትን የቴክኖሎጂ ውስንነቶች በመቅረፍ ሁሉንም ባንኮች ተሳታፊ ያደረገ ከደራሽ በተጨማሪ በቴሌብር አማራጭ እንዲከፍሉ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋቱ የአገልግሎት አሰጣጡን፣ የገቢ አሰባሰቡን እና የህግ ተገዥነት ስራዎች በማሳለጥ የታክስና ግብር ከፋዩን ጊዜና ወጪ በመቆጠብ ረገድ ውጤታማ ስራ ተሰርቷል::

ከመሰረተ ልማት ዝርጋታ ስራዎች አንጻር ሜክሲኮ አካባቢ የሚገኘው ብቸኛና ዋና ዳታ ማዕከል ውስጥ የሚገኙትን ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የኔትወርክ መሳሪያዎች በአዲስ ኮርስዊችና ቶፕ ኦፍ ራክ ስዊች መቀየሩ፣ የቆዩ ነባር ሰርቨሮችን በአዲስ መቀየራቸው፣ ነባር መተግበሪያዎች ላይ ማሻሻያ መደረጉ፣ UPS፣ AC፣ ጸረ ቫይረስ እና የደህንነት መሳሪያዎች (Antivires and Firewall)፣ ጀነሬተር እና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች መታደሳቸው የመረጃ ቅብብሎሽ ፍጥነት እንዲጨምር ያደረገና የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሳለጥ ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክት የተደረገው ባለፉት ሶስት ዓመታት በተሰሩ ስራዎች ነው:: ከውጤት አንጻር ለአብነት በኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት (eSW) ለአንድ ፈቃድ የሚወስደውን ጊዜ በአማካይ ከ15 ቀናት ወደ 2.5 ቀናት እንዲቀንስ በማድረግ ከ100 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ወጪ ማዳን ተችሏል::

ደጋፊ ስራዎችንም በቴክኖሎጂ እንዲመሩ ከማድረግ አንጻርም የጉምሩክ የሪከርድና ማህደር ዶክመንት ማኔጅመንት ሲስተም ተግባራዊ መደረጉ፣ የሰው ሀይል አስተዳደር ስራን ለማቀላጠፍ የሚያግዘው የኤሌክትሮኒክ የሰው ሀብት መረጃ አስተዳደር (HRM system) ተግባራዊ መደረጉ እና የቢሮ ደህንነት መቆጣጠሪያ ሲ.ሲ.ቲቪ. ካሜራ መዘርጋቱ ተጠቃሽ ስራዎች ናቸው::

ከቴክኖሎጂ አኳያ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከላይ የተጠቀሱት የገቢውን ዘርፍ ወረቀት አልባ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች በአውሮፓ ህብረት፣ በእንግሊዝ መንግስት፣ በዓለም ገንዘብ ድርጅት እና በዓለም ባንክ ድጋፍ በተቀጠሩና በውስጥ ባለሙያዎች የተከናወኑ ቢሆንም በሌላ በኩል የጉምሩክ ስራ አመራር

ስርዓት(eCMS) ተገቢው ርክክብ አለመፈጸሙ እና ከአልሚው ድርጅት ቋሚ የሆነ የቴክኒክ ድጋፍ ውል አለመኖሩ ዛሬ ላይ ለሚስተዋሉ ችግሮች ምንጭ መሆኑ፣ ለሲግታስ ስርዓት ከአልሚው ድርጅት ጋር የነበረው የቴክኒክ ድጋፍ ውል በመቋረጡ እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በመልቀቃቸው በሲስተሙ ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ ሳይደረግ መቆየቱ፣ በቂ የሆነ የመረጃ ማከማቻ አለመኖሩ እና የኔትወርክ እና የኤሌክትሪክ መቆራረጥ በዳታ ማዕከል ውስጥ ባሉ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ላይ ጉዳት ማድረሱና ለአገልግሎት አሰጣጡና ገቢ አሰባሰቡ ተግዳሮት መሆኑ ዋና ዋና ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ሲሆኑ በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን ዕቅዱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውጤታማነትን በማረጋገጥ የታክስና የጉምሩክ አስታዳደር ስርዓቱን በተሟላ ሁኔታ በመደገፍ ዲጅታል የሆነ የገቢ አስተዳደር ለመፍጠር የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ስራዎች መስራት ይጠይቃል።

## 2.2.5 የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ማረጋገጥ

የአገልግሎት አሰጣጡን ከማሻሻል እና የተገልጋዩን ዕርካታ ከማረጋገጥ አንጻር የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓትን ለማዘመን እንዲያስችል ተቋሙ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻልና ተግባራዊ በማድረግ፣ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አልምቶ ስራ ላይ በመዋል፣ የተቋሙን ሰራተኞች አቅም በመገንባት ከተገልጋዮች ጋር ተከታታይ ግንኙነት በመፍጠርና ችግሮችን በጋራ በመፍታት፣ የዜጎችን ቻርተርን በማሻሻልና ተግባራዊ ማድረግ እና በስጋት ስራ አመራር ላይ የተመሰረተ አገልግሎት በመስጠት ተግባራዊ በማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸም ዘመን አገልግሎት አሰጣጡ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን በማድረግ የደንበኞች ዕርካታ ለማሻሻል ጥረት የተደረገ ሲሆን ተቋሙ በየዓመቱ የደንበኞች ዕርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከተገልጋዮች ዕርካታ ደረጃ በመነሳት ለአገልግሎት አሰጣጥ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት የማሻሻያ ዕርምጃዎችን በመውሰድ በ2013 ከነበረው የ76 በመቶ የዕርካታ ደረጃ በ2015 ወደ 82 በመቶ ማሳደግ ተችሏል።

ይሁንና በዳሰሳ ጥናቶችና በተለያዩ የውይይት መድረኮች የሚለዩ ችግሮችን በፍጥነት መፍትሄ ከመስጠት፣ ከማስፈጸም አቅም ውስንነት እንዲሁም ከተዘረጉ የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች መቆራረጥ ጋር በተያያዘ የአግልገሎት አሰጣጡ የደንበኞች ዕርካታን በተሟላ ሁኔታ የተረጋገጠ እንዳይሆን አድርጓል። በመሆኑም በቀጣይ ሶስት ዓመት አሰራሮችን በማዘመን እና በቴክኖሎጂ በማደስገፍ፣ ተከታታይ የህግና የመመሪያ ማሻሻያ በማድረግ፣ ከደንበኞች ጋር ስትራቴጂክ ግንኙነት በመፍጠር እና የአመራርና የፈጻሚውን አቅም በመገንባት የደንበኞችን ዕርካታ በተጨባጭ ወደ ሚያረጋግጥበት ደረጃ ማድረስ ይገባል። የዚህ ዋና ተግባር ግምገማ የሚያሳየው አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና የደንበኞች ዕርካታ ለማረጋገጥ የአሰራር ስርዓት እና የቴክኖሎጂ ማሻሻያ ስራዎች ወሳኝነት ያላቸው በመሆኑ ይህ ዋና ተግባር ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ዋና ተግባር ውጤት በመሆኑ በስትራቴጂክ ዕቅዱ እንደ ዋና ተግባር ሊወሰድ የማይችል መሆኑ የግምገማ አፈጻጸሙ ያመላክታል።

## 2.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማህበረሰቡን በማስተማር ወደ ታክስ መረቡ የሚገቡትን ከመመዝገብ ጀምሮ በንግድ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ያሉ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስራዎች በህግ አግባብ መፈጸማቸውን የማረጋገጥና ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ተግባር ነው። የህግ ተገዥነት ሥራዎችን በአግባቡ መፈጸም በፈቃደኝነት ታክስና ቀረጥ የመክፈል ባህልን የማዳበር፣ የንግድ ፍትሀዊነትን የማስፈን እና የማህበረሰቡን ደህንነት የማስጠበቅ ዓላማዎችን ያሳካል።

## 2.3.1 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል

የታክስና ጉምሩክ ትምህርት ከማሳደግ አንጻር የተገልጋይ ተግባቦት መድረኮችን በመፍጠር፣ ከባለድርሻና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ጋር የተለያዩ መድረኮች በማዘጋጀት፣ የታክስና ጉምሩክ ህጎችን በሬድዮና በቴሌቪዥን በማስተላለፍ፣ የፓናል ውይይቶች በማድረግ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በኤሌክትሮንክስ ሚዲያ፣ በህትመት ሚዲያ በመጠቀም መረጃዎች ተደራሽ ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በ2013 ከነበረበት 811 የግብር ከፋዮች **የሞጁላር ሥልጠና** ያገኙትን በማሳደግ በ2015 14,040 ማድረስ ተችሏል፡፡ በትምህርት ቤቶችም ትውልድን በግብር ሥርዓት ላይ ከመቅረጽ አንጻር የታክስና ጉምሩክ ክበቦችን በማቋቋም እና በመደበኛ ትምህርት ግንዛቤ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራም ተከናውኗል፡፡

ከላይ በተገለጸው መሠረት የንግዱን ማህበረሰብ በማስተማር፣ በመከታተልና የህግ ማስከበር ስራ በመስራት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረው 41,396 የግብር ከፋዮች ቁጥር በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 59,404 ለማድረስ ታቅዶ 60,068 (101.12 በመቶ) ግብር ከፋዮች ደርሷል፡፡ የንግድ ትርፍ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ያስታወቁ ግብር ከፋዮች በአማካይ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 70 በመቶ ባለፉት ሶስት ዓመታት በአማካይ 76 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 82 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም በስትራቴጂክ ዕቅዱ በ2018 እንዲደረስበት የተቀመጠውን ዒላማ ማሳካት የተቻለ በመሆኑ በመካከለኛው ዘመን ዕቅድ የዒላማ ክለሳ ያስፈልጋል፡፡

የህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ ስጋትን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ የኦዲት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የቁጥጥርና ድጋፍ ተደራሽነትን የማስተካከል እና የኦዲት ሽፋንን ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ የኦዲት ሽፋን በ2012 ከነበረበት 9 በመቶ ወደ 14 በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ታክስ ግብር ይገባኛ እና ፍርድቤት የደረሱ ጉዳዮች ላይ ለመርታት እንዲያስችል የህግ ባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ፣ በታክስና ጉምሩክ ዙሪያ የዳኞችን ግንዛቤ በማሳደግ እና ቅንጅታዊ ስራ በማጠናከር የፍርደቤት የመርታት አቅም በመዝገብ በ2012 ከነበረበት 78 በመቶ ወደ 85 በመቶ በመድረሱ በስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀመጠውን ዒላማ ማሳካት ተችሏል፡፡

ከላይ የተገለፁ ስኬቶች ቢኖሩም ካለው ታክስ ከፋይ አንጻር የትምህርት ሽፋን በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ ታክስ ከፋዩ ባለበት ሆኖ ትምህርቱን የሚያገኝበት ኢ-ለርኒንግ አሰጣጥ ያለመኖር፣ የንግድ ትርፍ ግብር ከክፍያ ጋር የማስታወቅ አፈጻጸም በ2012 ከነበረበት 46 በመቶ በየዓመቱ እየቀነሰ በማምጣት 41 በመቶ በመድረሱ በመካከለኛ ዕቅድ ዘመን ዕቅድ መከለስ የሚጠይቅ መሆኑ፣ የኦዲት ሙያዊ ስነ-ምግባር ጉድለት መኖሩ፣ የሶስተኛ ወገን መረጃ ከማደራጀት፣ ለኦዲት ከመጠቀም እና የኦዲት ጥራት ከማረረጋገጥ አንጻር ውስንነቶች ተስተውለዋል፡፡

ስለሆነም የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ በታክስ ህጉና አሰራሮች ላይ ቀጣይነት ያለው የታክስ ከፋዮች ትምህርት በተለያዩ የትምህርት መስጫ ዘዴዎች መስጠት፣ የታክስ ክሊኒክ (Tax-Clinic) ፕሮግራም መዘርጋት፣ በኤሌክትሮኒክስ የማስተማሪያ ዘዴ (E-Learning) የሚሰጡ ትምህርቶችን በግብር ከፋዮች ዓይነትና ደረጃ ለይቶ በመተግበር የታክስ ትምህርት ሽፋኑም ማሳደግ፣ የንግድ ትርፍ ግብር ከክፍያ ጋር ማስታወቅን የሚያሳድግ አሰራርና ቴክኖሎጂ ቀርጾ መተግበር፣ የህቡዕ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ታክስ መረብ የሚገቡ ታክስ ከፋዮች ቁጥር ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ማድረግ እና የኦዲት ባለሙያዎች አቅምና ሙያዊ ስነ-ምግባር በማጎልበት እንዲሁም የሶስተኛ ወገን መረጃዎችን በመጠቀም የኦዲት ጥራትን ማረጋገጥ ይጠያቃል፡፡

## 2.3.2 የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል

የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ከማሻሻል አንጻር የአገልግሎት አሰጣጥና ቁጥጥር ሚዛናዊነት ለማስጠበቅ፣ የገቢ አሰባሰብ ውጤማነትን ለማሳደግ፣ ምቹ የንግድ እንቅስቃሴ ለመፍጠርና የህግ ተገዥነትን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። በዚሁ መሠረት የህግ ተገዥነት ማሻሻያ ስትራቴጂ በመቅረጽ ተግባራዊ መደረጉ፣ የስጋት መስፈርቶች ማሻሻልና ወቅታዊ የስጋት ፕሮፋይል ማዘጋጀት መቻሉ፣ በስጋት መርህ መሠረት ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶችን መርጦ ማስራጨት፣ የታክስ ከፋዮች የህግ ተገዥነት ደረጃ በመለየት ታማኝ የሆኑትን ዕውቅናና ሽልማት እንዲሰጣቸው መደረጉና ዝቅተኛ የህግ ተገዥነት ደረጃ ያላቸውን ታክስ ከፋዮች ለህዝብ ይፋ በማድረግ (Naming and Shaming) የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ አበረታች ውጤቶች ተመዝግዋል።

የጉምሩክ ስጋት ስራ አመራር ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 52 በመቶ ወደ 77 በመቶ በመፈጸም በስትራቴጂክ ዕቅዱ በ2018 እንዲደረስበት የተቀመጠውን ዒላማ የተሳካ በመሆኑ በቀጣይ በመካከለኛው ዘመን ዕቅድ የዒላማ ክለሳ ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ይጠቁማል። ይሁንና በሀገር ውስጥ ለኦዲት የተመረጡ የታክስ ከፋዮች ማህደራት ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 90.5 በመቶ ወደ 84 በመቶ የቀነሰ በመሆኑ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ይደርስበታል ተብሎ የተቀመጠውን የ92 በመቶ ዒላማ ማድረስ ባለመቻሉ በመካከለኛው ዘመን ዕቅድ የዒላማ ክለሳ ተደርጎ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ዒላማ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ የኦዲት አፈጻጸም መለካት ያለበት በማህደር አፈጻጸሙ እንጂ በሚገኝ ገንዘብ ባለመሆኑ ገንዘቡ ውጤት ተደርጎ መወሰድ ስላለበት በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት የፍሬ ግብር የገንዘብ መለኪያ እንዳይካተት ተደርጓል።

የስጋት ስራ አመራር ስራዎች ሀገሪቱ ልታጣ የነበረውን ገቢ ከማዳን በተጨማሪ የህግ ተገዥነትን በማሳደግ ረገድ የራሱን አስተዋጽዎ ያበረከተ ቢሆንም ዓለም ከደረሰበት ደረጃ ከማድረስ አንጻር ሥርዓቱ በአመዛኙ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፣ የመረጃ አቅርቦት እና ጥራት ችግሮች ያሉበት መሆኑ፣ የግንዛቤ ክፍተት በመኖሩ ስራዎችን በስጋት ያለመምራት የሚስተዋል በመሆኑ በቀጣይ በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሲሆኑ የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነትን በጥናት የሚረጋገጥበት አግባብ ሊኖር ይገባል።

## 2.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል

የታክስና የንግድ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድን በመከላከል ፍትሀዊ የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ስርዓት ለማስፈንና የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል። በዚሁ መሠረት የታክስ ማጭበርበርን ከመከላከል አንጻር የታክስ ኢንተለጀንስ እና ኢንቨስትጌሽን ኦዲት ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸው፣ የሀሰተኛ ደረሰኞች ምንጭ የሆኑ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽኖችን ማለትም ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሚሸጡ፡ ሃሰተኛ ደረሰኞችን አትመው የሚያሰራጩ፣ በመንግስት የተሰጡ መብቶችን ያለአግባብ የሚገለገሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ክትትልና ኦፐሬሽን በማድረግ አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ለፍትህ አካላት የማስተላለፍ ሥራ ተሰርቷል። በአጠቃላይ የንግድ ማጭበርብር መከላከል ውጤታማነትን ከማሳደግ አንጻር የኢንተለጀንስ ውጤታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከነበርበት 72 በመቶ በ2015 ወደ 78 በመቶ በማድረስ በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተያዘውን ዒላማ ማሳካት የተቻለ ቢሆንም የአፈጻጸም አመላካቹ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የጉምሩክና የታክስ ማጭበርበር ውጤታማንትን በሚያካተት መልኩ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር የህግ ዕቃዎች ማከማቻና መተላለፊያ አከባቢዎችን በጥናት የመለየት፣ ከፌዴራልና ክክልል የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት፣ የመቆጣጠሪያ ኬላዎችን አቅም በማጠናከር በአጠቃላይ ባለፉት ሶስት ዓመታት ብር 14.2 ቢሊዮን ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ተይዘዋል።

በስትራቴጂክ ዕቅድ የተያዘውን የኮንትሮባን መከላከል ውጤታማነት በ2012 ከነበረበት 63 በመቶ ወደ 70 በመቶ ማድረስ በመቻሉ የታቀደው ዒላማ ተሳክቷል።

ይሁንና የጉምሩክና ታክስ ማጭበርብርና ኮንትሮባንድን በሚፈለገው ደረጃ ከመከላከል አንጻር የህግ ተጠያቂነትን በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ የግብር ከፋዩ የህግ ተገዥነት በሚጠበቀው ደረጃ አለመድረሱ፣ ህግ ወጥነትን ለመከላከል የሚያስችል የግብዓት፣ የቴክኖሎጂና የመረጃ እጥረት መኖራቸው እና የቅንጅት ስራዎች ውጤታማነት አነስተኛ መሆኑ ውስንነቶች ተስተውለዋል።

በቀጣይ የመካከለኛ ዕቅድ ዘመን የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ፣ የህግ አስገዳጅነት ያለው፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ ችግሮችን ከመሰረቱ ሊፈታ የሚችል የኮንትሮባንድ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታና የአገሪቱን የግብይት ስርዓት ከጥሬ ገንዘብ ዝውውር ነጻ በማድረግ በባንክ ስርዓት ብቻ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችል የንግድ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል።

## 2.4 ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት

### 2.4.1 የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል

የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ኃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ከማድረግ አንጻር ባለፉት ሶስት ዓመታት ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ዋና ዋና የአገር ውስጥ በላድርሻ አካላትን በመለየትና ስትራቴጂክ አጋርነቱን በማሻሻል በታክስና በጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በህግ ተገዥነት ስራዎች፣ በቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ በመረጃ ልውውጥ እና በአቅም ግንባታ ስራዎችን በቅንጅት በመስራት ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል።

ይሁንና ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በቅንጅት ለመስራት የተደረገው እንቅስቃሴ ከውጤት አኳያ ሲታይ የተቀላጠፈ የታክስና የጉምሩክ አገልግሎት አሰጠጥ እንዲኖር ከማድረግ እና የንግድ ማጭበርበርን ከመከላከል አንጻር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። በተመሳሳይ ከመንግስት ተቋማት ጋር ያሉት ቅንጅታዊ አሰራሮች አስገዳጅነት የሌላቸው እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የማያስችሉ በመሆናቸው ንግድን ከማሳለጥ እና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር ውስንነቶች ተንጸባርቀዋል። በመሆኑም በመካከለኛ ዕቅድ ዘመኑ የአገር ውስጥ አጋር አካላት ትብብር በአገልግሎት አሰጣጥና በህግ ተገዥነት ስራዎች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

### 2.4.2 የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል

የታክስና የጉምሩክ አስተዳደርን ከማዘመን አንጻር ከውጭ አገር ተቋማት ጋር ማለትም የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት (WCO)፣ የዓለም ገንዘብ ድርጅት (IMF) ፣ የዓለም ባንክ (IFC) ፣ የእንግሊዝ የገቢና ቀረጥ ተቋም (HMRC) የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ጽ/ቤት (ACFTA)፣ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ኮሜሳ (COMESA)፣ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ቀጠና ጽ/ቤት ፣ የኮሪያ አለም አቀፍ ተራዶ ድርጅት (KOICA) ፣ የጃፓን ተራዶ ድርጅት (JICA) ፣ የቻይና የታክስ እና ጉምሩክ ተቋም (BRITACOM) ፣ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የታክስና ጉምሩክ አስተዳደሮች እና ሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት በአቅም ግንባታ፣ በመረጃ ፣ በተሞክሮ ልውውጥ እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ተደርጎ አዎንታዊ ውጤቶች ተገኝተዋል።

ይሁንና የአጋርነትና ትብብር ስራውን በአሰራር የተደገፈ በማድረግ ለታክስና ለጉምሩክ አስተዳደሩ ዘላቂ ጥቅም በሚያስገኝ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አንጻር ክፍተቶች ተስተውሏል። በመሆኑም በቀጣይ ሶስት ዓመታት

ከውጭ አገራትና ድርጅቶች ጋር በስትራቴጂ የሚመራ አሰራር በመቅረጽና የታክስና የጉምሩክ አስተዳደሩን ከማዘመን አንጻር ዘላቂ ጥቅሞች ሊያስገኙ በሚችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ በማተኮር መስራት ያስፈልጋል።

## 2.5 ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

### 2.5.1 የገቢ አፈጻጸም ግምገማ

የገቢው ዘርፍ ባለፉት ሦስት የልማት ዕቅድ ትግበራ ዓመታት (2013-2015) የተቋሙን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት፣ የአሰራር ስርዓቶችን በመቅረጽና በማሻሻል፣ የህግ ተገዥነት ስራዎችን በማጠናከር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ አጋርነትና ትብብሮችን በማሻሻል የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማነት በማረጋገጥ የመንግስትን የወጭ ፍላጎት ለመደገፍ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ከገቢ አሰባሰቡ አኳያ በየዓመቱ አበረታች የሆኑ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ከታች በቀረበው ግራፍ ለማሳየት እንደተሞከረው የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ምርት ያለው ጥምርታ በ2013 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.3 በመቶ ወደ በ2014 በጀት ዓመት 7.1 በመቶ እንዲሁም በ2015 በጀት ዓመት 7.3 በመቶ (በትንበያ የተደረሰበት) መሆኑን ያመለክታል። ስለሆነም የባለፉት ሶስት ዓመታት የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ምርት ጥምርታ ያለው አፈጻጸም በየዓመቱ እየወረደ የመጣ መሆኑን በመገንዘብ የገቢው ዘርፍ በቀጣይ በሚተገበረው የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ይሄንን አፈጻጸም የሚቀይር ስራ መስራት ይኖርበታል።

#### 2.5.1.1 የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ምርት ያላው ጥምርታ ግምገማ



### 2.5.1.2 የገቢው ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ




| | 2013 | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|
| አፈጻጸም (%) | 96.34 | 93.53 | 97.91 |
| ዓመታዊ ዕድገት (በቢሊዮን ብር) | 45.7 | 57.49 | 104.15 |
| ዓመታዊ ዕድገት (%) | 19.6 | 20.59 | 30.93 |

ከላይ እንደተገለጸው ያለፉት ሶስት ዓመታት የገቢ ዕቅድ አፈጻጸሙ በየዓመቱ ዕድገት እያሳየ የመጣ መሆኑን መረጃው ያመላክታል። ስለሆነም የገቢው ዘርፍ ይህንኑ አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታትም አጠናክሮ ማስቀጠል ይጠበቅበታል።

## 2.6 ባለፉት ሦስት ዓመታት የስትራቴጂክ ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት የአፈጻጸም ደረጃ አመላካቾች

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች | የአጸጸም ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መስኪያ | 2013 | 2014 | 2015 |
| 1 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት | | | | |
| 1.1 | የሰው ኃይል የመፈጸም ብቃትን ማሳደግ | | | | |
| 1.1.1 | የሠራተኛ ምርታማነት ማሳደግ | በመቶኛ | 22.31 | 26.83 | 18.01 |
| 1.1.2 | የሰራተኛ ዕርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | 54.40 | 48.30 | - |
| 1.2 | የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ | | | | |
| 1.2.1 | ወደ አመራር የመጡ የሴት ሰራተኞች ድርሻን ማሳደግ | በመቶኛ | 29.96 | 29.58 | 40.23 |
| 1.2.2 | የባለብዙ ዘርፍ አካታችነት አፈጻጸምን ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 65 | 70.00 | 73.00 |
| 1.3 | የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል | | | | |
| 1.3.1 | የኦዲት ግኝት ልዩነት ማስተካከል አፈጻጸምን ማሻሻል | በመቶኛ | 74.21 | 69.00 | 97.70 |
| 1.3.2 | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | በመቶኛ | 91.41 | 93.00 | 91.91 |
| 1.4 | የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት እና አጠቃቀም ማሻሻል | | | | |
| 1.4.1 | በስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነት ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 59.00 | 71.00 | 75.00 |
| 1.5 | ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል | | | | |
| 1.5.1 | የቀነሰ የስጋት ተጋላጭነት | በመቶኛ | 76.00 | 69.00 | 47.00 |
| 1.5.2 | የቀነሰ የስነምግባር ግድፈት | በመቶኛ | 2.95 | 4.00 | 1.51 |
| 1.6 | የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | | | | |
| 1.6.1 | የሀገር ውስጥ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነት ማሻሻል | ኢንዴክስ በመቶኛ | | | |
| 1.7 | የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል | | | | |
| 1.7.1 | የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነትን ማሻሻል | ኢንዴክስ በመቶኛ | | | |
| 1.8 | የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸምን ማሻሻል | | | | |
| 1.8.1 | የተገልጋዮች ዕርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | 75.63 | 79.50 | 81.80 |
| 2 | ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት | | | | |
| 2.1 | የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት | | | | |
| 2.1.1 | የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸምን ማሻሻል | ኢንዴክስ | | | |

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች | የአጻጸም ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | 2013 | 2014 | 2015 |
| | | በመቶኛ | | | |
| 2.2 | **የአሠራር ስርዓት አፈጻጸምን ማሻሻል** | | | | |
| 2.2.1 | በስታንዳርድ መሠረት የተመዘገቡ ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 99.10 | 99.80 | 99.98 |
| 2.2.3 | በኢ-ታክስ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 48.32 | 58.00 | 81.00 |
| 2.2.5 | በስታንዳርድ መሠረት ኦዲት የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | | 85.80 | 95.60 |
| 2.2.6 | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ክሊራንስ ያገኙ ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | | 84.60 | 117.06 |
| 2.2.7 | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ተመላሽ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 91.60 | 91.00 | 96.50 |
| 2.2.8 | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ቅሬታ የታየላቸው ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 93.00 | 94.00 | 102.11 |
| 2.2.9 | በወቅቱ የተዘጉ የገቢ ሂሳቦች | በመቶኛ | 95.00 | 98.00 | 99.80 |
| 2.2.10 | በስታንዳርድ መሠረት የተፈጸመ የገቢ ትልልፍ | በመቶኛ | 100.00 | 100.00 | 100.00 |
| 2.2.11 | በስታንዳርድ መሠረት የተሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶች | በመቶኛ | 95.57 | 96.18 | 95.41 |
| 2.2.12 | በፍርድ ቤት የመዝገብ መርታት አቅም ማሳደግ | በመቶኛ | 64.90 | 84.70 | 89.55 |
| 2.3 | **የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል** | | | | |
| 2.3.1 | በስጋት መሠረት የተመረጡ የታክስ ከፋዮች ማህደራት ውጤታማነት ማሳደግ | በመቶኛ | 78 | 85 | 84 |
| 2.3.2 | የጉምሩክ ሥጋት ሥራ አመራር ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 62.00 | 69.00 | 77.00 |
| 2.4 | **የመረጃ አስተዳደር አፈጻጸምን ማሻሻል** | | | | |
| 2.2.4 | በኢ-ታክስ የከፈሉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | በመቶኛ | 15.00 | 28.50 | 38.00 |
| 2.4.1 | የመረጃ አስተዳደር አፈጻጸም ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 93.80 | 91.80 | 89.50 |
| 2.4.2 | የኢንተለጀንስ ውጤታማነት ማሳደግ | በመቶኛ | 48.00 | 61.03 | 61.50 |
| 3 | **የግብር ከፋዮችን የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻል** | | | | |
| 3.1 | **የታክስ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል** | | | | |
| 3.1.1 | ወደ ታክስ መረቡ የገቡ ግብር ከፋዮች | በቁጥር | 45,282.00 | 50,467.00 | 54,627.00 |
| 3.1.2 | በፈቃደኝነት የተከፈለ የታክስ ገቢ ድርሻን ማሳደግ | በመቶኛ | 77.91 | 81.50 | 88.47 |
| 3.1.3 | የንግድ ትርፍ ግብር በወቅቱ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 68.30 | 79.00 | 79.00 |
| 3.1.4 | የተ.እ. ታ በወቅቱ ያሳወቁ ታክስ ከፋዮች በመቶኛ | በመቶኛ | 71.40 | 80.60 | 84.00 |
| 3.1.5 | የንግድ ትርፍ ግብር ከክፍያ ጋር ያሳወቁ ግብር ከፋዮች | በመቶኛ | 50.36 | 44.00 | 41.00 |
| 3.1.6 | የተ.እ.ታ ከክፍያ ጋር ያሳወቁ ታክስ ከፋዮች | በመቶኛ | 43.50 | 37.00 | 39.00 |
| 3.1.7 | የታክስ ኦዲት ሽፋን ማሳደግ | በመቶኛ | 25.97 | 28.30 | 28.32 |
| 3.1.8 | በታክስ ኦዲት በልዩነት የተወሰነ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 21.10 | 19.20 | 17.64 |

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች | የአጻጸም ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | 2013 | 2014 | 2015 |
| 3.2 | የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል | | | | |
| 3.2.1 | የኮንትሮባንድ መከላከል ውጤታማነት ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 56.00 | 70.00 | 70.00 |
| 4 | ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | | | | |
| 4.1 | ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | | | | |
| 4.1.1 | አጠቃላይ የታክስ ገቢ ዕቅድ በቢሊዮን ብር | በቢሊዮን ብር | | | |
| 4.1.2 | የታክስ ገቢ ለሀገራዊ ምርት ያለው ጥምርታ በመቶኛ | በመቶኛ | 8.30 | 7.10 | 7.30 |
| 4.1.3 | የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 60.00 | 55.60 | 61.80 |
| 4.1.4 | የፌደራል ገቢ በቢሊዮን ብር | በቢሊዮን ብር | 279.44 | 336.71 | 440.86 |
| 4.1.5 | የፌደራል ታክስ ገቢ ለሀገራዊ ምርት ያለው ጥምርታ በመቶኛ | በመቶኛ | 6.43 | 5.47 | 5.57 |
| 4.1.6 | የፌደራል ታክስ ገቢ ከሀገራዊ ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 69.35 | 63.54 | 47.05 |
| 4.1.7 | የሀገር ውስጥ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 59.70 | 58.27 | 61.44 |
| 4.1.8 | የጉምሩክ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 40.24 | 41.73 | 38.56 |
| 4.1.9 | የታክስ አስተዳደር ወጪ (100 ብር ለመሰብሰብ) | በብር | 1.55 | 1.60 | 1.17 |
| 4.1.10 | የተከማቸ የታክስ ዕዳ በዓመት ውስጥ ከተሰበሰበው የታክስ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | በመቶኛ | 17.14 | 16.80 | 11.53 |

# 3 የገቢው ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች

የገቢው ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድን ለማሳካት የሚያስችሉ የዕቅዱ ታሳቢዎች፣ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችና ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት እንዲሁም የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎች እና ዋና ዋና ተግባራት

**ሰንጠረዥ 1፡ የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

| ርዕይ | በ2022 ዘመናዊ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በቀረጥና ታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት | |
|---|---|---|
| **ስትራቴጂያዊ ግቦች** | **ተልዕኮ** | **ዕሴቶች** |
| 1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት<br>2. የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ<br>3. የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ<br>4. ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት<br>5. ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የታክስና ጉምሩክ አገልግሎት በመስጠት ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን በመከላከልና በመቆጣጠር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ | 1 አገልጋይነት<br>2 መሰጠት<br>3 ሙያዊ ብቃት<br>4 ታማኝነት<br>5 በቡድን መስራት |

| ግብ 1: ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት | |
|---|---|
| • የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | • የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል<br>• ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል |
| **ግብ 2: የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ** | |
| • ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻል<br>• ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም | • የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ |
| **ግብ 3: የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ** | |
| • የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል<br>• የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል | • የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል |
| **ግብ 4: ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት** | |
| • የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | • የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነትን ማሳደግ |
| **ግብ 5: ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ** | |

## 3.2 የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ታሳቢዎች

በዚህ ክፍል ለገቢው ዘርፍ የ2016-2018 የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ እንደ መነሻ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሀገራዊ የመካከለኛ ዘመን (2016-2020) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ እንደ አንድ መነሻ የተወሰደ ሲሆን የመንግስትን የፊሲካል አቋም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ የሚቻለው አስተማማኝ ከሆነው የመንግስት ቀረጥና ታክስ ገቢ ምንጭ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ አማራጭ የሌለው መሆኑ በመንግስት ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ የማሻሻያ ስራዎችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ዋናው የፊሲካል ታሳቢ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

### 3.2.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ታሳቢዎች

በስትራቴጂክ ዘመኑ የአገሪቷ አጠቃላይ ኢኮኖሚ በማክሮ ኢኮኖሚ ፊሲካል ማዕቀፍ ላይ በተገለጸው መሰረት በየዓመቱ የሚያድግ መሆኑ፣ የገቢ ዕቃዎች በየአመቱ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እየተሻሻለ እንደሚሄድ እና የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡን እንደሚያሻሽሉ በታሳቢነት ተወስደዋል፡፡

- በማዕቀፍ ዘመኑ (2016-2018) ኢኮኖሚው ዕድገት እንደሚኖረው፣
- በአሁኑ ወቅት የዋጋ ንረቱ በተከታታይ ተጠናክሮ በሚወሰድ የፊሲካል ፖሊሲ፣ የገንዘብ ፖሊሲ፣ የዋጋ ማረጋጊያ እርምጃዎች እና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚሰሩ ስራዎች እየቀነሰ እንደሚመጣ፣

### 3.2.2 የታክስ ፖሊሲ ታሳቢዎች

በታክስ ፖሊሲ ረገድ ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ በትግበራና በመጽደቅ ሂደት ላይ ካሉት የህግ ማሻሻያዎች ባሻገር ያልታዩ አማራጮችን ግምት ውስጥ ለማስገባት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ፣

- **በትግበራ እና በመጽደቅ ሂደት ላይ ያሉ፣** የማህበራዊ ድጋፍ ታክስ (Social Welfare Development Duty Tax) ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ህግ ማሻሻያ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ ማሻሻያ እና የተሽከርካሪ ቀረጥ ነጻ መመሪያ ማሻሻያ ይገኙበታል፡፡
- **አዳዲስ ከዚህ ቀደም ያልታዩ አማራጮች፣** በዚህ ረገድ በግብር ህጉ ያልታቀፉ አዳዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችንም በማጥናት በህጉ እንዲታቀፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚችሉ ለስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅቱ በታሳቢነት ታይቷል፡፡

### 3.2.3 የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች

የቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ የታክስና ጉምሩክ ህግን በመጣል ብቻ የሚሻሻል ሳይሆን በህግ የተጣለውን ቀረጥና ታክስ በሚገባ በስራ ላይ የሚያውል ጠንካራ ተቋም ሲገነባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት የገቢው ዘርፍ አቅምና አቋም እንዲሁም በቀጣይ አደረጃጀቱን በመፈተሽ የሚያስፈልጉ ወሳኝ ማሻሻያዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህም ረገድ በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ነገር ግን ቀረጥና ታክስ የማይከፍሉ የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዘርፍ ውስጥ የሚሳተፉ የኢኮኖሚ ተዋናዮችን በመለየት በቀረጥና ታክስ ስርዓቱ ማስገባት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ማሻሻያ ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የገቢው ዘርፍ የሰው ኃይል፣ ተቋማዊ አቅም፣ የአሰራር ችግሮችን እና አደረጃጀቱን እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡን በጥልቀት በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችልና በተግባር ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መነሻ የሚወሰዱ የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ለገቢ አሰባሰቡ ዋና ቁልፍ ጉዳይ መሆናቸውን በመገንዘብ የታክስ አስተዳደሩ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የቀረጥና ታክስ ገቢ ለመሰበሰብ ወይም በየስትራቴጂክ ዘመኑ የተቀመጡትን ዒላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ የገቢ ፊሲካል ስራዎች በልዩ ትኩረትና ርብርብ መስራት የሚጠበቅበት ይሆናል፡፡

- በታክስና ጉምሩክ አስተዳደሩ ረገድ ትኩረት ከተደረገባቸው ማሻሻያዎች መካከል **የኦዲት አፈጻጸም ማሻሻያ፣ የቀረጥና ታክስ ዕዳ አሰባሰብ ፣ የመረጃ አስተዳደር ፣ የንግድ ማጭበርበርና የኮንትሮባንድ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን አፈጻጸም ማሻሻል** እንዲሁም የህግ ማስከበር ስራዎችን አጠናክሮ የማስቀጠል ማሻሻያዎች እንደሚደረጉ ይጠበቃል፣
- የታክስ አሰባሰቡን ለማዘመን የተጀመሩ **የጉምሩክና ታክስ አስተዳደር ስርዓት** ተግበራትን ማለትም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር፣ ዜጎች ቀረጥና ታክስን **በፈቃደኝነት የመክፈል** ባህላቸው እንዲዳብር **የጉምሩክና ታክስ ትምህርትን የማስፋፋት**፣ የቀረጥና ታክስ ንቅናቄ በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ይሰራል፡፡

## 3.3 ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች

በመካከለኛ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የገቢው ዘርፍ የለያቸውን ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ይሆናል፡፡

### ➲ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ

የዚህ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ ዓላማ ቀረጥና ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማዳበር ሲሆን ይህንንም ለማሳካት የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ በመቅረጽ መተግበርን የሚያጠቃልል ነው፡፡ አቅጣጫው ቀረጥና ታክስ ከፋዩን በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማር፣ በመደገፍ እና ዕውቅና በመስጠት አብዛኛው ቀረጥና ታክስ ከፋይ በፈቃደኝነት ግዴታውን እንዲወጣ ማስቻል ሲሆን የህግ ተገዥነት ባህሪ ለውጥ ማምጣት ባልቻሉ አካላት ላይ ተመጣጣኝ የህግ ማስከበር ተግባር ተፈጻሚ የሚደረግበት ነው፡፡

### ➲ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት

ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓት የመገንባት አቅጣጫ ታሳቢ የሚያደርገው አጠቃላይ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ዓለም በደረሰበት የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲደገፍ ማድረግን ነው፡፡ ይህ የዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓት ለአገልግሎት ተቀባዩ ግልጽ፣ ቀላል፣ ተገማች እና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት፣ የህግ ተገዥነትና አስተዳደራዊ ወጪ በመቀነስ እና የተገልጋዩን ዕርካታ በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ የገቢውን ዘርፍ ተልዕኮ ማሳካት ነው፡፡

### ➲ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ

በኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ፣ በህገ ወጥ ንግድ፣ በቀረጥና ታክስ ማጭበርበር እና በኮንትሮባንድ ምክንያት ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ ለመሰብሰብ አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት የንግዱ ማህበረሰብ በዕኩልነት

ተወዳዳሪ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኖ የቆየና በሀገሪቱ ያለውን የሃብት ክፍፍል ኢ-ፍትሀዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም የገቢው ዘርፍ ይሄንን ተግዳሮት ለማስተካከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ወደ ታክስ መረቡ ያልታቀፉትን እንዲታቀፉ በማድረግ እነዲሁም የቀረጥና ታክስ ህጎችን በሁሉም ቀረጥና ታክስ ከፋዮች ላይ በእኩል ደረጃ ተፈጻሚ በማድረግ የቀረጥና ታክስ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም በመካከለኛ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የህግ ማስከበር ስራዎችን በማጠናከር እንዲሁም ከአጋር እና ተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ኢፍታዊነትን በመከላከል የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ ለመሰብሰብ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### ➲ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር

የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለአንድ ዓላማ በጋራ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ይህ አቅጣጫ የቴክኒክ፣ የዕውቀት ሽግግር፣ የመረጃ ልውውጥ፣ ህገወጥነትን የመከላከል አሰራር መዘርጋትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጋር አካላትን መለየት፣ ግንኙነት እና ስምምነት በመፍጠር በስምምነቱ መሰረት ለመፈጸም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና ማነቆዎችን በጋራ ለይቶ በመፍታት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

### ➲ የዳበረ የስራ ባህል ማምጣት

የታክስ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶችን የተላበሰ እና ሁለንተናዊ አቅሙን በመገንባት የዳበረ የስራ ባህል ያለው የሰው ኃይል ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይህ አቅጣጫ የሰው ኃይል ስራ አመራር ልማት ስትራቴጂ ከመቅረጽ ጀምሮ፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መሳብና ማቆየት፣ የምዘና፣ የማትጊያ እና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ ታማኝና ለስራ ተነሳሽ የሆነ አመራር እና ፈጻሚ ማፍራትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

# 4 የመካከለኛ ዘመን (2016 — 2018) የልማት ዕቅድ ግቦች ፣ ዋና ዋና ተግባራትና ዒላማዎች

## 4.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት

ይህ ስትራቴጂክ ግብ ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ለመገንባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ተግባራትን ያካተተ ሲሆን በስሩ የሰው ሀብት መሳብ፣ ማቆየት ፣ ብቃት ማሳደግን፣ የሀብት አጠቃቀም እና ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ ተቋማዊ ስጋት ስራ አመራር ማጠናከርን ፣ የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎች ውጤታማነት ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው::

### 4.1.1 የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ

**መግለጫ**

የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር ውጤታማነት ማሳደግ ማለት ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባና የረካ አመራርና ፈጻሚ በመፍጠር የተቋሙን ምርታማነት ማሻሻል ነው::

**ዝርዝር ተግባራት**

የአመራሩን ክህሎት ማሳደግ ፣ የሰራተኛውን ብቃት መገንባት፣ ጠንካራ የስራ ባህል መገንባት፣ የሰራተኛ ደህንነትና ጤንነት የሚጠበቅበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈና ውጤታማ የመረጃ አያያዝና የምዘና ስርዓት መገንባት፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ ሰራተኛን በመሳብና በማቆየት እና ዕርካታውን በማረጋገጥ ምርታማነቱን ማሳደግን ያጠቃልላል::

**ውጤት:- የረካና ምርታማነቱ ያደገ ሰራተኛ**

### 4.1.2 የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ

**መግለጫ**

የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ማለት ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ሀብት እንዲመደብ የማድረግና የተመደበውን ሀብት በውጤታማነት ማስተዳደር ነው::

**ዝርዝር ተግባራት**

የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የግዥ ፍላጎትን መለየት እና ጥራቱን የጠበቀ ግዥ መፈጸምና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፣ የቋሳዊ ሀብቶችንና የግብዓቶች አቅርቦትና አስተዳደር አፈጻጸምን ማሻሻል፣ በበጀት አጠቃቀም ዙሪያ ከተቆጣጣሪ አካላት በሚቀርቡ ግኝቶች ላይ ወቅታዊ ማስተካከያ ማድረግን ይጨምራል::

**ውጤት፦ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም**

### 4.1.3 የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል

**መግለጫ**

የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል ማለት በዓለም ዓቀፍ ህጎች እና መንግስት በሴቶችና በወጣቶች፣ በህጻናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ፣ የጤና ፣ የበጎ አድራጎትና

ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች፣ አካባቢ ጥበቃ ስራዎች፣ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ያወጣቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መመሪያዎችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበሩ ማድረግ ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

በዚህ ዋና ተግባር ስር ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችን እና የኤች. አይ. ቪ. ኤደስ ጉዳዮችን በተመለከተ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎችን ትኩረት ሰጥቶ በዕቅድ ውስጥ አካቶ መተግበርን፣ የሴቶች አመራር ሰጪነት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን፣ የተቋሙ አመራር እና ሰራተኞችን በማስተባበር የጤና፣ የአረንጓዴ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ማከናወንን፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ለሚጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረግን ያካትታል፡፡

**ውጤት፦ ያደገ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች ውጤታማነት**

### 4.1.4 ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል

**መግለጫ**

ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር ማለት በተቋም ደረጃ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን አስቀድሞ በመለየት የስጋት መጠኑን በመቀነስ ተቋማዊ ጤንነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

ይህን ተግባር ለማሳካት የሚከናወኑ ስራዎች የስጋት መከላከያ ስትራቴጂ ወቅታዊ ማድረግ፣ ተቋማዊ ስጋቶችን በየጊዜው ከተለዋዋጥ ሁኔታዎች አንጻር መለየት ፣ መተንተን ፣ ድረጃ ማውጣት፣ በተቋም ደረጃ የተለዩ ስጋቶችን ለመቀነስ ኃላፊነት የሚውስዱ ባለቤቶችን መለየት፣ የስጋት ስትራቴጂውን መተግበር እና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን ያጠቃልላል፡፡

**ውጤት፡- የቀነሰ የስጋት ተጋላጭነት**

## 4.2 የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ

የታክስና የጉምሩክ አሠራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ ማለት የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽ፣ ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፣ የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ እና ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ አሠራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ ልህቀትን ማረጋገጥ ነው፡፡ የአሰራር ልህቀትን ለማምጣት ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻል፣ የቴክኖሎጂ ልማትና አጠቃቀምን የማሳደግ፣ የመረጃ አስተዳደር ስርዓትን የመዘርጋት እና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት እንዲሁም በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋትን ያጠቃልላል፡፡

### 4.2.1 ቀጣይነት ያለው የህግና የአሠራር ስርዓት ማሻሻያ

**መግለጫ**

ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻል ማለት የታክስና የጉምሩክ የህግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን በመቅረጽና በማሻሻልን የላቀ አገልግሎት ለመስጠት፣ የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ እና የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግን የሚያካትት ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ፣ የጉምሩክ አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያዎችን መቅረጽና በማሻሻል በሚመለከተው አካል ማጸደቅን ፤ የኢ-ኮሜርስ ንግድ ስርዓትን ለማሳለጥ የሚያስችል የታክስና የጉምሩክ አሰራር ስርዓት፣ የታክስና የጉምሩክ ኦፕሬሽናል አሰራሮችን ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አድርጎ ማሻሻልና መቅረጽ፣ የህግ ተገዥነት አሰራሮች የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከልን በሚያስችል መልክ ማሻሻልና መቅረጽን እንዲሁም ተግባራዊ የተደረጉ ህግ፣ መመሪያና አሰራሮች ውጤታማነት በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብን የሚያጠቃልል ነው።

አገልግሎት አሰጣጥን ከማሳለጥ አንጻር ለተገልጋዩ በቀጥታ /Online/ አገልግሎት የሚያገኝበት ስርዓትን ማሻሻል፣ የአገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት፣ ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት መዘርጋትና ማሻሻል፣ የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ጥናት (Time Release Study) ማካሄድ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ስምምነት ሰነድ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ፣ የመረጃ አቅርቦት ማዕከሎችን (Contact Center) አፈጻጸም ማሻሻል፣ የደንበኞች አቀባበልና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት፣ ለተገልጋዩ እንደየ ባህሪው እና ደረጃው ልዩ አገልግሎት ማግኘት የሚችልበት የአገልግሎት ስርዓት መዘርጋት፣ ዓለም ዓቀፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ልህቀት ዕውቅና ማግኘት እና የተገልጋይ እርካታ ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው።

**ውጤት፦ የላቀ የአሰራር ስርዓት ፣ ያደገ የተገልጋይ እርካታ**

### 4.2.2 ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም

**መግለጫ**

ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም ማለት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮ መነሻ በማድረግ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኢንቨስትመንትን ለመደገፍና ለማበረታታት፣ ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን በማጐልበት፣ በፌደራልና በክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች ጋር ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በመፍጠር በሀገር ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ማጣጣምን ያካትታል።

**ዝርዝር ተግባራት**

የታክስ አስተዳደር ተግባራትን በፌደራል እና በክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች በሁሉም ዕኩል ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ የክልሎችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ቀርጾ መተግበር። በሀገር ደረጃ የታክስ አስተዳደሩ በመረጃ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ጠንካራ የመረጃ ቅብብሎሽና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት፣ በክልል በሚገኙ የፌደራል ገቢ ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤቶችና በክልል የገቢ ባለስልጣናት መካከል በህግ ማስከበር፣ በግብር ከፋዮች ትምህርትና ድጋፍ፣ በአቅም ግንባታና በሌሎች የታክስ ጉዳዩች የጋራ ስምሪት ማድረግና የገቢ አሰባሰቡን ማሻሻል፣ ከክልል የገቢ ሰብሳቢና የፋይናንስ ዘርፍ ተቋማት ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርዓት (ማለትም የምክክር መድረኮችን) በመዘርጋት የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር አፈጻጸሞችን በጋራ መገምገም፣ መፍትሄ ማስቀመጥና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የጋራ ገቢዎች እና በዊዝሆልዲንግ ስርዓት የሚሰበሰቡ ግብርና ታክሶች በወቅቱ ወደ ገቢው ባለቤቶች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማጠናከር ወጥ የሆኑ የስልጠና ካሪኩለሞችን ማዘጋጀት ናቸው።

**ውጤት፦ የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር**

### 4.2.3 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል ማለት ለታክስና ጉምሩክ አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ምንጮችን መለየት፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ማጥራትና ማደራጀት፣ መተንተን፣

ማስራጨትና ጥቅም ላይ ማዋልን፣ ለቀረጥና ታክስ ውሳኔዎች የተሰራጩ መረጃዎች ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት የመረጃ ደህንነትን ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ ስራ ላይ ማዋልን፣ የተቋሙን የመረጃ ምንጭ ማስፋትና የጥራት ደረጃውን ማሳደግን፣ የመረጃ ልውውጡን በቴክኖሎጂ ማስደገፍን፣ ለቀረጥና ታክስ ውሳኔ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ውጤታማነት እያሳደጉ መሄድን፣ ቀጠናዊና ዓለም ዓቀፋዊ የመረጃ ትስስር መፍጠርን፣ የኢንተለጀንስ መረጃዎችን መጋራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ደህንነትና ጥራት ማስጠበቅ፣ ትልልቅ መረጃዎችን ለመተንተን /Big Data Analysis/ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣ የጉምሩክ ላብራቶሪ መገንባት፣ የመረጃ ማከማቻ ማዕከል መገንባት እና የተቋሙን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በአርተፊሺያል ኢንተለጀንስ ማስደገፍን፣ የሀገር ውስጥ ታክስና ጉምሩክ መረጃ ቅብብሎሽን ማሳደግን ያጠቃልላል፡፡

**ውጤት፡- የላቀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና አጠቃቀም**

### 4.2.4 የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ

**መግለጫ**

የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ ማለት ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለህግ ማስከበር ስራዎች፣ ለገቢ አሰባሰቡ ውጤታማነት እና ሌሎች የተቋሙን የአሠራር ስርዓቶች የሚደግፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመግዛት፣ የማልማት፣ የማስተዳደር፣ የመጠቀም እና የማሻሻል ስራዎችን የሚያካትት ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የቀረጥና ታክስ ገቢ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመቀየር የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ማለትም አዲስ የዳታ ማዕከል (Data Center) መገንባት፣ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል (Disaster Recovery Data Center) መገንባት፣ ለመረጃ ደህንነት የሚረዱ ፖሊሲዎችን በስራ ላይ ማዋል፣ ያሉትን የመረጃ መሰብሰቢያና ማደራጃ ሶፍትዌሮችን ማሻሻል፣ ተጨማሪ የመረጃ ቋቶች (Databases) መመስረት፣ በስራ ላይ ያለውን የሲግታስ (SIGTAS) ስርዓት ኢ-ማሳወቅና ኢ-ክፍያ (e-TAX) በያዘ መልኩ ሙሉ በሙሉ Webbased በሆነ አዲስ ቴክኖሎጂ መተካት፣ የተከፋፈሉ ስርዓቶችን (Sub Systems) እርስ በእርስ እንዲናበቡና እንዲቀናጁ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ማለትም የክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ ተቋማት፣ ኢትዮቴሌኮም፣ የኢንፎርሜሽን ደህንነት መረብ አስተዳደር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ባንክና ንግድ ባንኮች ጋር ለክፍያና ለመረጃ ልውውጥ የሚያገለግሉ ኢንተርፌሶች በተመሳሳይ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተዳደሩ ማድረግ፣ ግብር ከፋዩ በቀጥታ የሚያቀርባቸውን የአገልግሎት ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ የመተግበሪያ ሶፍትዌሮች (Applications) ማሻሻልና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ በማልማት በስራ ላይ ማዋል፣ የታክስና የጉምሩክ የቴክኖሎጂ ስርዓቶች ሙሉ በሙሉ ለመረጃ ቅብብሎሽ ማስተሳሰር (Interface)፣ በስራ ላይ የነበረውን የካርጎ ስካኒንግ ስርዓት በዘመናዊ ቴክንሎጂ መተካት፣ የካርጎ ትራኪንግ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት (eCMS) ማሻሻል፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት (eSW) ሁለተኛ ምዕራፍን ማጠናቀቅና ተግባራዊ ማድረግ፣ የጉምሩክ ዋጋ ዳታቤዝ(ECVS-G2) ሲስተምን ማሻሻል፣ የቢዝነስ ኢንተለጀንስ እና ዳታ አናሊቲክስ ስርዓት መዘርጋት፣ የጉምሩክ ዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር ማስገቢያ(VDD)

ማሻሻል፣ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚረዳ ከVDD ጋር የሚሰራ የተሽከርካሪ ማረጋገጫ ስርዓት(VVS) ስርዓት ማሻሻል ይጠቀሳሉ፡፡

በተጨማሪም አሁን በስራ ላይ ያለውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ (CRM) ስርዓት ሙሉ በሙሉ በኢ-ኢንቮይስ (e-Invoice) ስርዓት መቀየር፣ የእጅ በእጅ ደረሰኝ መከታተያ ስርዓት ማሻሻል፣ ያሉትን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች መከታተያ (FD) ማሻሻል፣ የገበያ ዋጋ ማስገቢያ ስርዓት ማሻሻል፣ በስራ ላይ ያለውን ዳታዌር ሃውስ (DWH) በአዲስ አሰራርና ቴክኖሎጂ መቀየር፣ የጣት አሻራ ስርዓት ከብሔራዊ መታወቂየ (TIN/ FAYDA-ID) ጋር ማስተሳሰር፣ የጥሪ ማዕከል ስርዓትን የማሻሻል ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የኮርፖሬት ስራዎችን ወረቀጥ አልባ ለማድረግ የሚያግዙ የኢንተርፐራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ (ERP) ማለትም የሰው ሃብት አስተዳደር (HRMS)፣ የግዥ አስተዳደር ስርዓት (PMS)፣ የፔይሮል ሲስተሙን ከኢፊሚስ ሲስተም ጋር ማስተሳሰር፣ የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት (FAM) ከኢፊሚስ ሲስተም ጋር ማስተሳሰር፣ የተሽከርካሪ መከታተያ (Fleet Management) እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ የመልክት መለዋወጫ(Username@mor.gov.et) ማሻሻል፣ የተቋሙ ድረ ገጽ(www.mor.gov.et) እና (www.ecc.gov.et ) ማሻሻል፣ በጅምር ላይ ያለውን ኤሌክትሮኒክ ዶክመንት አስተዳደር (EDMS) ሙሉ በሙሉ መተግበር፣ የውስጥ ለውስጥ የመረጃ ቴክኖሎጂ አስተዳደር ስርዓት (ITSM) ማሻሻልናየመተግበር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

**ውጤት፡ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ውጤታማ አሠራሮች**

## 4.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

ሀገራዊ የታክስና ጉምሩክ ገቢ በላቀ ሁኔታ ለማሳደግ የህግ ተገዥነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን የሚወስኑ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቢኖሩም የገቢ ሰብሳቢው ተቋም የማስፈጸም ብቃት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ተቋሙ በአደረጃጀቱና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በመጠቀምና ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ውጤታማ የህግ ተገዥነት ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ለማዳበር፣ የንግድ ፍትሀዊነትን ለማስፈን፣ የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃት እንዲሰበሰብ ያስችላል፡፡ በመሆኑም የታክስ ከፋዮች ትምህርት ለማጠናከር፣ የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ለማሳደግ፣ የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ለማሻሻል እና አስተማሪ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

### 4.3.1 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸም ማሻሻል ማለት ታክስ ከፋዮች በታክስ ህጉ መሰረት የንግድ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳዩ ሰነዶች በወቅቱ በማቅረብ የሚጠበቅባቸውን የታክስ ግዴታ በፈቃደኝነት እንዲወጡ ማስቻልን የሚያካትት ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የታክስ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ለማሻሻል የትምህርት ስትራቴጂ ማሻሻል እና መተግበርን፣ ትምህርቱ ያመጣውን ፋይዳ በመገምገም ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግን፣ ወደ ታክስ መረቡ መግባት ያለባቸውን ታክስ ከፋዮች ወደ ታክስ መረቡ ማስገባትን፣ ታክስ በወቅቱ እና በትክክል አሳውቀው መክፈላቸውን ማረጋገጥን፣ የኦዲት ስትራቴጂ በማሻሻልና በመተግበር የኦዲት ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ በፍርድ ቤት

የመርታት አቅም ማሳደግን ፣ ለታክስ ህጉ ተገዥ የሆኑትን በመለየት ዕውቅናና ሽልማት እንዲሁም ልዩ አገልግሎት በመስጠት በፈቃደኝነት የሚከፈለውን የታክስ ገቢ ድርሻን ማሳደግን ያካትታል።

**ውጤት፦ ያደገ የህግ ተገዥነት**

### 4.3.2 የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል ቀረጥና ታክስ ከፋዮችን እንደየ ስጋት ባህርያቸው በመለየት ለህግ ተገዥ የሆኑትን ማበረታታትና የላቀ አገልግሎት በመስጠት፣ ተገዥ ያልሆኑትን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት በመከላከል የህግ ተገዥነትን በማሳደግ የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግ ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ማሻሻልና በተሟላ ሁኔታ መተግበር፣ የስጋት ፕሮፋይል ማደራጀትና ወቅታዊ ማድረግ፣ የስጋት መመዘኛ መስፈርቶች ልየታ ሥርዓት ማሻሻል፣ ስጋቶችን መለየትና መተንተን፣ የስጋት ደረጃ ማውጣትና በስትራቴጂው መሰረት ማስተናገድ፣ የስርዓቱ ውጤታማነት በመገምገምና የማስተካከያ ዕርምጃ በመውሰድ የአገልግሎት አሰጣጥና የቁጥጥር ሚዛናዊነት በጠበቀ መልኩ መመራቱን ማረጋገጥን ያካትታል።

**ውጤት፦ ያደገ የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነት**

### 4.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ለማሻሻል የታክስና ጉምሩክ ህግና የአስተዳደር ሥርዓት የማይፈቅድ ህገወጥ ተግባራት ላይ ከተሰማሩ አካላት ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ወደ ህጋዊ መስመር መመለስ የሚችሉት ወደ ታክስ መረቡ እንዲገቡ ማገዝ፣ ከጥፋታቸው መታረም ያልቻሉትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት አስተዳደራዊና ህጋዊ ዕርምጃ በመውሰድ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡና ሌሎችም እንዲማሩበት ማድረግን የሚጨምር ሥራዎችን ማከናወን ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

በታክስ ማጭበርበር፣ በኮንትሮባንድና በተለያዩ ህገወጥ ተግባራት ላይ የተሰማሩትን በማስተማር እንዲመለሱ ማድረግ፣ በኢንተለጀንስ ክትትል፣ በድንገተኛ ፍተሻ፣ በኢንቨስትጌሽን ኦዲት እና በወንጀል ምርመራ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንደ የጥፋት ደረጃቸው አስተማሪ የሆነ ህጋዊ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው በማድረግ የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ ያካትታል።

ኮንትሮባንድና ንግድ ማጭበርበር ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ስጋት በማይሆኑበት ደረጃ ለመቀነስ ተቋማዊ የመከላከል አቅምን ማጠናከር፣ ከፌዴራል ተቋማት፣ ከክልሎች አደረጃጀቶች፣ ከጎረቤት ሀገራት እና አለም አቀፍ የህግ ማስከበር ተቋማት ጋር ቅንጅት መፍጠር፣ በኮንትሮባንድ አስከፊነትና ጉዳት ዙሪያ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣ የኮንትሮባንድ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ሕጋዊ የኢኮኖሚ አማራጭ እንዲኖረው ማድረግ እና የኮንትሮባንድ መከላከል ሥራውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ ያስፈልጋል።

**ውጤት፡- የቀነሰ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ**

## 4.4 ስትራቴጂ አጋርነት ልህቀት

ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት ከሀገር ውስጥና ከውጪ አጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ ነው። በዚህ የትኩረት መስክ የቅንጅት ስትራቴጂ መቅረጽ፣ አጋር አካላትን መለየት እና ተግባራዊ ማድረግን የሚያካትት ነው። በዚህ መሰረት ከሀገር ውስጥ አጋር አካላት ጋር በህግ ማስከበር፣ በድንበር አስተዳደር፣ በታክስ ማጣጣም፣ በህጎች ዝግጅት፣ በሰው ኃይል አቅም ግንባታና ቅንጅት፣ በመረጃ ልውውጥ እና በቴክኖሎጂ ትስስር ላይ የሚያተኩር ሲሆን በተመሳሳይ ከውጪ አጋር አካላት ጋር በቴክኒክ ድጋፍ፣ በዕውቀት ሽግግር፣ በልምድ ልውውጥ ላይ በማተኮር በጋራ ተቀናጅቶ በመስራት ውጤታማነትን ማረጋገጥ ታሳቢ ያደረገ የትኩረት መስክ ነው።

### 4.4.1 የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል

**መግለጫ**

የሀገር ውስጥ አጋር አካላት ትብብር ማሻሻል ማለት ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት ቁልፍ ሚና ካላቸው የባለድርሻ አካላት ማለትም ከተቆጣጣሪ አካላት፣ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር፣ ከፌዴራል ተቋማት፣ ከንግድና ሙያ ማህበራት ጋር ቅንጅት በመፍጠር አገልግሎቱን በማሳለጥ፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድ መከላከልን ያጠቃልላል።

**ዝርዝር ተግባራት**

ከአገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት የሚፈጥረባቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮችን እና ቅንጅቱ የሚፈጠርባቸውን አካላት መለየት እና በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል ነው።

**ወጤት፡ የተፈጠረ ውጤታማ ቅንጅት ፣ የተፈቱ ችግሮች**

### 4.4.2 የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነት

**መግለጫ**

የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነት ማጠናከር ማለት ተቋሙ ተልኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ከውጭ ሀገራት፣ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የቴክኒክ ድጋፍ እና ተሞክሮ ማግኘት የሚያስችል ትብብር መፍጠርን የሚያካትት ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የውጭ አገራት አጋር አካላት ድጋፍና ትብብር አንጻር ተቋሙ ተልኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ትብብር መፍጠር አስፈላጊ የሆነባቸውን የውጭ ሀገራት፣ ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችን፣ የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶችን የመለየት፣ ትብብር በመፍጠር የጉምሩክ እና የታክስ የሁለትዮሽ እና የብዝዮሽ ስምምነት የመፈራረም፣ በአህጉራዊ እና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች ላይ በመሳተፍ ለተቋሙ ጥቅም በሚያስገኙ ጉዳዮች ላይ መደራደር እና በተፈጠሩ ግንኙነቶች የተገኙ የቴክኒክ ድጋፎች ውጤታማ መሆናቸው ማረጋገጥን የሚጠይቅ ነው።

**ውጤት፡- የተፈጠረ ውጤታማ ግንኙነት፣ የተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ**

## 4.5 ዘላቂ ገቢ ዕድገትን ማረጋገጥ

መንግስት የቀረጸው የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ሊሳካ የሚችለው የታክስ ገቢ በብቃት መሰብሰብ የሚያስፈልግ መሆኑ ዕሙን ነው። ይሁን እንጂ አሁን የሚታየውን የሀገሪቱን የተዳከመ የፊሲካል አቋም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ የሚቻለው አስተማማኝ ከሆነው የመንግስት ታክስ ገቢ ምንጭ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህም የሀገር ውስጥ ሃብትን ውጤታማ በሆነ መንገድ አሟጦ መጠቀም አማራጭ የሌለው ሲሆን ለዚህም የታክስ ገቢ አሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ በሀገር ደረጃ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሥራዎችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ዋናው የፊሲካል ታሳቢ ተደርጎ ተወስዷል።

ይህም በቀጣይ በሙሉ አቅም ወደ ትግበራ ይገባሉ ተብለው የታሰቡ የታክስ ዓይነቶች የማህበራዊ ደህንነት ልማት ቀረጥ ግብር (Social welfare development duty tax) ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ህግ ማሻሻያ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ ማሻሻያ፣ እና የተሽከርካሪ ቀረጥ ነጻ መመሪያ ማሻሻያ፣ እና አዳዲስ ከዚህ ቀደም ያልታዩ አማራጮች በቀጣይ እንደሚሰራባቸውና ወደ ትግበራ እነደሚገቡ ይታሰባል። ከዚህም በተጨማሪ በግብር ህጉ ያልታቀፉ አዳዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችንም በማጥናት በህጉ እንዲታቀፉ ለማድረግ ሥራዎችን ለማከናወን ታሳቢ ተደርጓል።

### 4.5.1 ዘላቂ ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

በዚህ ግብ ስር ከቀረጥና ታክስ የሚሰበሰበውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ስራዎችን ወደ ተግባር በመቀየር ውጤታማነቱን በገቢ አሰባሰብ ማረጋገጥ ሲሆን ይህም ከለይ ባሉ ግቦች ማለትም ተቋማዊ የማስፈጸም አቅምና የሀብት አጠቃቀምን በማጎልበት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ አጋርነትን በማጠናከር ፣ ታክስና የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ልህቀትን በማረጋገጥ እና የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት በማሻሻል ከቀጥታ ታክሶች፣ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰበውን ገቢ ማሳደግ ነው።

በዚሁ መሰረት በፍቃደኝነት ከሚከፈለው ገቢ በተጨማሪ የገቢ ፊዚካል ስራዎች ማለትም ከአሰስመንት ፣ ከውዝፍ ዕዳ እና ከተወረሱና ከተያዙ ንብረቶች ሽያጭ አፈጻጸምን በማሻሻል የሚገኝ ገቢን ማሳደግ ነው።

**ውጤት፡- ያደገ ገቢ**

## 4.6 2016 — 2018 የተቀመጡ ግቦች

### 4.6.1 ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

| ስትራቴጂክ ግብ | ዋና ዋና ተግባራት | ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች | መለኪያ | መነሻ /2015/ | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| ስትራቴጂክ ግብ | ዋና ዋና ተግባራት | ጥቅል የፌደራል ገቢ ዕቅድ | ቢሊዮን ብር | 440.86 | 515.5 | 640 | 827 |
| | | የተጣራ የፌደራል ገቢ ዕቅድ | ቢሊዩን ብር | 347.97 | 440.83 | 594.45 | 766.70 |
| | | የሀገር ውስጥ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ | መቶኛ | 61.44 | 58 | 59 | 60 |
| | | የጉምሩክ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ | መቶኛ | 38.56 | 42 | 41 | 40 |
| | | የታክስ አስተዳደር ወጪ (100 ብር ለመሰብሰብ) | ብር | 1.17 | 1.31 | 1.21 | 1.06 |

### 4.6.2 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

| ስትራቴጂክ ግቦች | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ (2015) | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ | የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ማሻሻል | ወደ ታክስ መረቡ የገቡ ግብር ከፋዮች | በቁጥር | 60,068 | 67,309 | 75,609 | 84,325 |
| | | የታክስና ጉምሩከ ትምህርት ሽፋን ማሳደግ | በቁጥር | 2,000 | 2,500 | 3,600 | 7,200 |
| | | በፈቃደኝነት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ገቢ ድርሻን ማሳደግ | መቶኛ | 75 | 78 | 80 | 83 |
| | | በወቅቱ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | መቶኛ | 89 | 90 | 92 | 95 |
| | | በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | መቶኛ | 84 | 85 | 86 | 88 |
| | | በወቅቱ የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | መቶኛ | 95 | 96 | 97 | 98 |
| | | በወቅቱ አሳወቀው የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚከፍሉ የግብር ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | መቶኛ | 41 | 45 | 50 | 57 |
| | | በወቅቱ አሳውቀው የተ/እ/ታ ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ | መቶኛ | 39 | 43 | 45 | 48 |

| ስትራቴጂክ ግቦች | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ (2015) | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| | | ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | | | | | |
| | | በወቅቱ አሳውቀው የኤክሳይዝ ታክስቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | መቶኛ | 69 | 72 | 74 | 80 |
| | | የኦዲት ሽፋን በመቶኛ | መቶኛ | 26 | 28 | 30 | 32 |
| | | የኦዲት ስራዎች ጥራት ውጤታማነት | መቶኛ | 70 | 72 | 74 | 76 |
| | | በፍርድ ቤት የመዝገብ መርታት አቅም ማሳደግ | መቶኛ | 85 | 86 | 88 | 90 |
| | የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ማሻሻል | በስጋት መሠረት የተመረጡ የታክስ ከፋዮች ማህደራት ውጤታማነት | በመቶኛ | 84 | 93 | 94 | 95 |
| | | የጉምሩክ ሥጋት ሥራ አመራር ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 77 | 80 | 82 | 84 |
| | የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል | የኮንትሮባንድ መከላከል ውጤታማነት ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 70 | 73 | 77 | 80 |
| | | የታክስና ጉምሩክ ማጭበርበር ቁጥጥር ውጤታማነት ማሳደግ | ኢንዴክስ በመቶኛ | 78 | 80 | 82 | 84 |

## 4.6.3 የታክስና ጉምሩክ አሰራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ

| ስትራቴጂክ ግቦች | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ (2015) | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| የታክስና ጉምሩክ አሰራር ስርዓት ልህቀትን ማረጋገጥ | ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻል | የተቀረጸና የተሻሻለ የህግና የአሰራር ስርዓት | መቶኛ | | 70 | 75 | 80 |
| | | በስታንዳርድ መሰረት የተሰጡ አገልግሎቶች | በመቶኛ | 86 | 88 | 90 | 92 |
| | | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 82 | 84 | 86 | 88 |
| | | የሎተሪ አስተዳደር አፈጻጸም ውጤታማነት | በመቶኛ | | 85 | 90 | 92 |

| ስትራቴጂክ ግቦች | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ (2015) | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| | ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም | የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸም ውጤታማነት | ኢንዴክስ | 78 | 80 | 85 | 90 |
| | የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል | የመረጃ አስተዳደር ውጤታማነት | ኢንዴክስ | 89.5 | 91 | 93 | 95 |
| | የቴክኖሎጂ ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ | በስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 75 | 85 | 90 | 93 |

## 4.6.4 ስትራቴጂክ አጋርነት ልህቀት

| ስትራቴጂክ ግብ | ዋና ዋና ተግባራት | ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች | መለኪያ | መነሻ /2015/ | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| ስትራቴጂክ አጋርነት | የሀገር ውስጥ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነትን ማሳደግ | የሀገር ውስጥ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 78 | 82 | 85 | 88 |
| | የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነትን ማሳደግ | የውጭ ትብብር አፈጻጸም ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 64 | 70 | 75 | 80 |

## 4.6.5 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም

| ስትራቴጂክ ግቦች | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ (2015) | ዓመታዊ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2016 | 2017 | 2018 |
| ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የሀብት አጠቃቀምን ማጎልበት | የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ | ያደገ የሠራተኛ ምርታማነት | በሚሊዮን ብር | 33 | 37 | 44 | 54 |
| | | ያደገ የሰራተኛ ዕርካታ | በመቶኛ | 48 | 65 | 70 | 80 |
| | | የሰው ሀብት አስተዳደር ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 83 | 87 | 90 | 93 |
| | የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | የበጀት አፈጻጸም | በመቶኛ | 92 | 95 | 97 | 98 |
| | | የፕሮጀክት አፈጻጸም ውጤታማነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 50 | 70 | 75 | 80 |
| | | የኦዲት ግኝት ማስተካከል አፈጻጸም | በመቶኛ | 60 | 80 | 85 | 90 |
| | የባለብዙ ዘርፍ እና ማህበራዊ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል | ያደገ የባለብዙ ዘርፍ አካታችነት | ኢንዴክስ በመቶኛ | 73 | 76 | 80 | 83 |
| | | ያደገ የበጎ አድራጎትና የማህበረሰብ አገልግሎት | ኢንዴክስ በመቶኛ | የለም | 85 | 87 | 90 |
| | ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል | የቀነሰ የስጋት ተጋላጭነት | በመቶኛ | 47 | 55 | 48 | 41 |
| | | የቀነሰ የስነምግባር ግድፈት | በመቶኛ | 1.5 | 1.1 | 0.9 | 0.8 |

# 5 የመካከለኛ ዘመን ኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች

የገቢ ዘርፍ ለመካከለለኛ ዘመን የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ (2016-2018) ትግበራ የ10 ዓመቱንና በቀጣይ ሶስት ዓመታት ለሚተገበር የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚያገለግሉ አራት ፕሮግራሞችን ማለትም የስራ አመራር ድጋፍ፣ የህግ ተገዥነት፣ የታክስ መረጃ እና ቴክኖሎጂ፣ የታክስ መረጃ ቴክኖሎጂ፣ ገቢ አሰባሰብ እንደዲሁም በስራቸው ንዑስ ፕሮግራሞች በመቅረጽ የሚገመተውን ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ወጪ ግምት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 5.1 የመካከለኛ ዘመን የኢንቨስትመንት ፍላጎት

| የፕሮግራም ዝርዝር | የንዑስ ፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የኢንቨስተመንት ወጪ ግምት (በብር) | የፕሮጀክቱን የሚተገብር ተቋም | የፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ክልል | የፕሮጀክቱ አተገባበር ዘዴ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስራ አመራርና ድጋፍ | የግንባታ ስራዎች | 1 | ሐዋሣ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 427,211,247.00 | ገቢዎች | ሐዋሣ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 2 | አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 348,780,702.00 | ገቢዎች | አዳማ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 3 | ጂማ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 440,810,708.00 | ገቢዎች | ጂማ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 4 | ምዕራብ አ/አ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ እድሣት እና የማማከር አገልግሎት | 375,375,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 5 | ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ዕድሣት እና የማማከር አገልግሎት | 229,750,546.00 | ገቢዎች | ድሬደዋ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 6 | ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 326,891,289.00 | ገቢዎች | ባህር ዳር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 7 | መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 487,108,813.00 | ገቢዎች | መቀሌ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 8 | ከፍተኛ ግብር ዘፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 4,325,578,168.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 9 | ምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 4,325,578,168.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 10 | መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ፣ተያኝና የማማከር አገልግሎት | 4,325,578,168.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 11 | የሰሜን ምዕራብ ቢሮ ግንባታ ቢሮ ግንባታ፣ተያኝና የማማከር የማማከር አገልግሎት | 4,325,578,168.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 12 | የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ፣ ዲዛይን እና የማማከር አገልግሎት | 4,327,600,000.00 | ገቢዎች | ኮምቦልቻ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 13 | ተቋማዊ ስልጠና ማእከል እና የጉምሩክ ላ/ ግንባታ እና | 6,015,326,096.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት | ነባር |

| የፕሮግራም ዝርዝር | የንዑስ ፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የኢንቨስተመንት ወጪ ግምት (በብር) | የፕሮጀክቱን የሚተገብር ተቋም | የፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ክልል | የፕሮጀክቱ አተገባበር ዘዴ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የማማከር አገልግሎት | | | | በጀት | |
| | | 14 | የዋናው መ/ቤት የህንጻና ምድረግቢ የማስዋብ ግንባታ እና የማማከር አገልግሎት | 640,577,069.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (ITAS) ማሻሻያ ኘሮግራም | 15 | ሲግታስን በአዲስ መተካት፣ ኢ-ኢንቮይስ ፣ዳታ ዌር ሃውስ ሶፍትዌር ልማት፣ ቢዝነስ ኢንተለጀንስ እና ዴታ አናሊቲክስ ልማት (Data Modeling and Big Data Analysis) ፣ የዳታ ማዕከል እና የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል ግንባታ፣ | 3,780,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | የተካሄዳ የግንባታ ስራዎች | 16 | Enetprise Resource Planning | 10,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 17 | የታክስና ጉምሩክ የኤሌክትሮኒክ (E-learning) ትምህርት ስርዓት መዘርጋት | 15,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 18 | የማንዋል ደረሰኝ ትክክለኛነት ማረጋገጫ ስርዓት | 10,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 19 | በስራ ላይ ያለውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ስርዓት ማሻሻል | 200,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 20 | ታክስ ክሊኒክ | 20,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 21 | የሰው ኃብት ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር፣ | 25,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 22 | የተቋሙን እና የሠራተኛ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ | 10,000,000.00 | ገቢዎች | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ኣዲስ |
| | | 27 | ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 672,228,003.28 | ጉምሩክ | ኦሮሚያ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 28 | አዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 388,223,002.13 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 29 | ጎንደር መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 265,498,922.61 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 30 | ሻሁራ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 67,530,923.54 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 32 | ሠራቫ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 51,767,551.28 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 33 | ዶሮ ግብር መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 36,828,556.64 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 34 | ምድረ ገነት መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 81,920,000.00 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 35 | አርበረከቴ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 81,648,710.16 | ጉምሩክ | ኦሮሚያ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 36 | አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 244,710,360.85 | ጉምሩክ | ኦሮሚያ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 37 | ኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 175,818,716.61 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |

| የፕሮግራም ዝርዝር | የንዑስ ፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የኢንቨስተመንት ወጪ ግምት (በብር) | የፕሮጀክቱን የሚተገብር ተቋም | የፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ክልል | የፕሮጀክቱ አተገባበር ዘዴ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 38 | ኮንሶ መቆጣጠሪያ ጣቢያና ተያያዥ ግንባታዎች | 134,005,675.54 | ጉምሩክ | ደቡብ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 39 | ሰመራ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 5,430,969,782.11 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 40 | ሌይ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,717,017,501.36 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 41 | ወረታ መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 365,000,000.00 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 42 | ሳንጃ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 43 | አዋሽ ኬላ 7 ጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ | 13,614,737.50 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 44 | ኩርሙክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 45 | ጊዘን መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 46 | ሰርዶ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 47 | ጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና መኖሪያና ቤት እድሳት | 170,000,000.00 | ጉምሩክ | አፋር | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 48 | ቶጎጫሌ መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 200,000,000.00 | ጉምሩክ | ሱማሌ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 49 | የዋናው መ/ቤት ጋራዥና ተያያዥ ግንባታ | 365,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 50 | የዋናው መ/ቤት ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | 7,000,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 51 | መቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,200,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 52 | ዛላንበሳ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 53 | ሁመራ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 200,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 54 | ራማ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 160,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 55 | ሉግዲ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 56 | ዲማ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 150,000,000.00 | ጉምሩክ | ትግራይ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 57 | መተማ መቅረጫ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 250,000,000.00 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 58 | ሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,200,000,000.00 | ጉምሩክ | ሲዳማ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 59 | ባህርዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,200,000,000.00 | ጉምሩክ | አማራ | የመንግስት በጀት | አዲስ |

| የፕሮግራም ዝርዝር | የንዑስ ፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የኢንቨስተመንት ወጪ ግምት (በብር) | የፕሮጀክቱን የሚተገበር ተቋም | የፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ክልል | የፕሮጀክቱ አተገባበር ዘዴ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 60 | ጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | 1,000,000,000.00 | ጉምሩክ | ጅማ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 61 | ድሬደዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | 1,200,000,000.00 | ጉምሩክ | ድሬደዋ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት | 62 | የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት | 728,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 62 | የጉምሩክ ኤሌክትሮኒክስ ስራ አመራር ስርዓት (ECMS) ማሻሻያ | 15,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | | 63 | የጉምሩክ ዋጋ መተመኛ እና የዋጋ መረጃ መቀበያ ስርአቶች (EVS_G2 እና VDD_G2) ማሻሻል | 5,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | ነባር |
| | በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሰራሮች | 64 | የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት ሶፍትዌር ልማት ፕሮጀክት - ምዕራፍ 2 | 840,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 65 | የጉምሩክ ኢንተርፕራይዝ አርኪቴክቸር እና ዳታ ማጣጣም ፕሮጀክት | 56,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 66 | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ- ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት | 224,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 67 | የድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ኮሜርስ ፕሮጀክት | 168,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 68 | ዘመናዊ የካርጎ ስካኒንግ ግንባታና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት | 3,272,773,800.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 69 | ዘመናዊ የምድር ሚዛን መሰረተ ልማት ግንባታና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት | 10,200,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ፣ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 70 | የፍትሐብሄር ጉዳዮችና ተያያዥ የክትትል ስራዎች በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ | 12,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 71 | የኦዲት ስራን በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ ፕሮጀክት | 12,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 72 | የስው ሰራሽ አስተውሎትን መሰረት ያደረገ ቻትቦት፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎች እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ፕሮጀክት | 10,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 73 | የሰው ሰራሽ አስተውሎትን መሰረተ ያደረገ የመንገደኞች ስጋት ስራ አመራር ፕሮጀክት | 10,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 74 | ዘመናዊ የጉምሩክ ድንበር አስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት ፕሮጀክት | 600,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 75 | የጉምሩክ ላብራቶሪ ማቋቋም፣ | 1,500,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| | | 76 | ከአዋሳኝ ሀገሮች ጋር የአንድ አለቅ ፕሮጀክቶችን /One Stop Border Post / ማጠናቀቅ*፣ | 450,000,000.00 | ጉምሩክ | አዲስ አበባ | የመንግስት በጀት | አዲስ |
| ፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልጋቸው አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ወጪ | | | | 78,660,300,385.61 | | | | |

## 5.2 የዝርዝር ዓመታዊ የኢንቨስትመንት ዒላማዎች በፕሮጀክቶች

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| ስራ አመራርና ድጋፍ | 1 | ሐዋሣ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | 117,671,086.70 | 309,540,160.30 | - | - | 427,211,247.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 2 | አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | 121,513,473.40 | 227,267,228.60 | - | - | 348,780,702.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 3 | ጂማ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | 88,052,193.00 | 109,735,463.00 | 121,511,526.00 | 121,511,526.00 | 440,810,708.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 4 | ምዕራብ አ/አ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ እድሣት | - | 375,375,000.00 | - | - | 375,375,000.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 5 | ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ዕድሣት | - | 229,750,546.00 | - | - | 229,750,546.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 6 | ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | 122,241,311.00 | 52,916,096.00 | 100,866,941.00 | 50,866,941.00 | 326,891,289.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 7 | መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | 44,174,813.00 | 180,978,000.00 | 130,978,000.00 | 130,978,000.00 | 487,108,813.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 8 | ከፍተኛ ግብር ዘፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | - | 1,510,889,083.00 | 1,395,889,083.00 | 1,418,800,002.00 | 4,325,578,168.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 9 | ምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | - | 556,394,542.00 | 1,006,394,542.00 | 1,006,394,542.00 | 2,569,183,626.00 | 1,756,394,542.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 10 | መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ግንባታ | | 1,511,394,542.00 | 1,081,394,542.00 | 1,081,394,542.00 | 3,674,183,626.00 | 651,394,542.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 11 | የሰሜን ምዕራብ ቢሮ ግንባታ ቢሮ ግንባታ | - | 806,394,542.00 | 1,006,394,542.00 | 1,006,394,542.00 | 2,819,183,626.00 | 1,506,394,542.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 12 | የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታና ዲዛይን | - | 759,400,000.00 | 276,900,000.00 | 276,394,542.00 | 1,312,694,542.00 | 3,014,905,458.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 13 | ተቋማዊ ስልጠና ማእከል እና የጉምሩክ ላ/ ግንባታ | - | 1,803,831,524.00 | 1,403,831,524.00 | 1,403,831,524.00 | 4,611,494,572.00 | 1,403,831,524.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 14 | የዋናው መ/ቤት የህንጻና ምድረግቢ የማስዋብ ግንባታ | 138,118,348.00 | 502,458,721.00 | - | - | 640,577,069.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| የፌደራል ታክስ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም | 15 | የፌደራል ታክስ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም | - | 500,000,000.00 | 500,000,000.00 | 500,000,000.00 | 1,500,000,000.00 | 2,000,000,000.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 16 | አዲስ ሲግታክስ | | 500,000,000.00 | 945,000,000.00 | 945,000,000.00 | 2,390,000,000.00 | 1,390,000,000.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 17 | ኢ ለርኒግ | | 15,000,000.00 | - | - | 15,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 18 | የደረሰኝ ትክክለኛነት ማረጋገጫ | | 10,000,000.00 | - | - | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 19 | የካሽ ሪጅስተር ማሸሽያ | | 250,000,000.00 | 450,000,000.00 | 150,000,000.00 | 850,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 20 | ታክስ ክሊኒክ | | 20,000,000.00 | - | - | 20,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 21 | የታክስ ኪዎክስ | | 10,000,000.00 | - | - | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 22 | የሰው ኃብት ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር፣ | | 25,000,000.00 | - | - | 25,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| ስራ አመራርና ድጋፍ | 23 | የተቋሙን እና የሠራተኛ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ | | 10,000,000.00 | - | - | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 24 | የመረጃ መጠባበቂያ ማዕከል (Disaster Recovery Center) ማቋቋም፣ | | 250,000,000.00 | 350,000,000.00 | 250,000,000.00 | 850,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 25 | የData Modeling and Big Data Analysis ስርዓት መዘርጋት፣ | | 150,000,000.00 | 350,000,000.00 | 150,000,000.00 | 650,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 26 | የዳታ ማዕከል (Data Center) መገንባት፣የመረጃ መጠባበቂያ ማዕከል | | 350,000,000.00 | 400,000,000.00 | 500,000,000.00 | 1,250,000,000.00 | 250,000,000.00 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | | (Disaster Recovery Center) ማቋቋም እና የመረጃ ደህንነት መሠረተ ልማት (IT Security Infrastructure) መዘርጋት፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| | 27 | የትምህርትና የተግባቦት ስትራቴጂ መቅረጽ እና መተግበር | | 15,000,000.00 | - | - | 15,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 28 | ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 95,906,658.39 | 220,900,000.00 | 355,572,594.89 | | 576,472,594.89 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 29 | አዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 69,119,728.71 | 190,000,000.00 | 129,103,273.42 | | 319,103,273.42 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 30 | ጎንደር መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 44,071,082.74 | 150,000,000.00 | 71,427,839.87 | | 221,427,839.87 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 31 | ሻሁራ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 17,000,000.00 | 50,530,923.54 | | | 50,530,923.54 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 32 | ሠራቫ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 17,000,000.00 | 34,767,551.28 | | | 34,767,551.28 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 33 | ዶሮ ግብር መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 11,048,566.99 | 25,779,989.65 | | | 25,779,989.65 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 34 | ምድረ ገነት መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 24,576,000.00 | 57,344,000.00 | | | 57,344,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 35 | አርበረከቴ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 24,494,613.05 | 57,154,097.11 | | | 57,154,097.11 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 36 | አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 25,000,000.00 | 100,000,000.00 | 119,710,360.85 | | 219,710,360.85 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኋላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | 37 | ኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 52,745,614.98 | 123,073,101.63 | | | 123,073,101.63 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 38 | ኮንሶ መቆጣጠሪያ ጣቢያና ተያያዥ ግንባታዎች | 40,201,702.66 | 93,803,972.88 | | | 93,803,972.88 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 39 | ሰመራ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,629,290,934.63 | 200,000,000.00 | 500,000,000.00 | 700,000,000.00 | 1,400,000,000.00 | 2,401,678,847.48 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 40 | ሌይ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 515,105,250.41 | 200,000,000.00 | 300,000,000.00 | 125,956,125.48 | 625,956,125.48 | 575,956,125.48 | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 41 | ወረታ መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 1,469,384.12 | 130,000,000.00 | 170,000,000.00 | 63,530,615.88 | 363,530,615.88 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 42 | ሳንጃ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 365,388.21 | 80,000,000.00 | 69,634,611.79 | | 149,634,611.79 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 43 | አዋሽ ኬላ 7 ጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ | 3,614,737.50 | 10,000,000.00 | | | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 44 | ኩርሙክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 3,245,596.08 | 70,000,000.00 | 76,754,403.92 | | 146,754,403.92 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 45 | ጊዘን መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 3,284,596.08 | 80,000,000.00 | 86,715,403.92 | | 166,715,403.92 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 46 | ሰርዶ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 3,220,596.08 | 70,000,000.00 | 76,779,403.92 | | 146,779,403.92 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 47 | ጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና መኖሪያና ቤት እድሳት | 3,625,706.54 | 70,000,000.00 | 76,374,293.46 | | 146,374,293.46 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 48 | ቶጎጫሌ መቅረጫ ጣቢያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | 4,667,720.62 | 110,000,000.00 | 85,332,279.38 | | 195,332,279.38 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 49 | የዋናው መ/ቤት ጋራዥና ተያያዥ ግንባታ | | 25,000,000.00 | 170,000,000.00 | 170,000,000.00 | 365,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 50 | የዋናው መ/ቤት | | 80,000,000.00 | 3,000,000,000.00 | 1,500,000,000.00 | 4,580,000,000.00 | 2,420,000,000.00 | | | የፌዴራል | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | | ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | | | | | | | | | በጀት | | | | | |
| | 51 | መቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 400,000,000.00 | 310,000,000.00 | 710,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 52 | ዛላንበሳ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 90,000,000.00 | 60,000,000.00 | 150,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 53 | ሁመራ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 100,000,000.00 | 100,000,000.00 | 200,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 54 | ራማ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 80,000,000.00 | 80,000,000.00 | 160,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 55 | ሉግዲ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 70,000,000.00 | 80,000,000.00 | 150,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 56 | ዲማ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 70,000,000.00 | 80,000,000.00 | 150,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 57 | መተማ መቅረጫ ጣቢያ ቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | | 110,000,000.00 | 140,000,000.00 | 250,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 58 | ሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | 20,000,000.00 | 445,000,000.00 | 735,000,000.00 | 1,200,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 59 | ባህርዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | | 20,000,000.00 | 445,000,000.00 | 735,000,000.00 | 1,200,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 60 | ጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | | 20,000,000.00 | 377,421,875.00 | 602,578,125.00 | 1,000,000,000.00 | - | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 61 | ድሬደዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | | 20,000,000.00 | 445,000,000.00 | 735,000,000.00 | 1,200,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት | 62 | የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት | | 200,000,000.00 | 240,000,000.00 | 288,000,000.00 | 728,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | 63 | የኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ አንድ መስኮት ሶፍትዌር ልማት ፕሮጀክት - ምዕራፍ 2 | | 294,000,000 | 252,000,000 | 294,000,0000 | 840,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 64 | የጉምሩክ ኢንተርፕራይዝ አርኪቴክቸር እና ዳታ ማጣጣም ፕሮጀክት | | 19,600,000.00 | 16,800,000.00 | 19,600,000.00 | 56,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 65 | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት | | 78,400,000.00 | 672,000,000.00 | 78,400,000.00 | 224,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| ስራ አመራርና ድጋፍ | 66 | የድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ኮሜርስ ፕሮጀከት | | 58,800,000.00 | 50,400,000.00 | 58,800,000.00 | 168,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 67 | ዘመናዊ የካርጎ ስካኒንግ ግንባታና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት | | 3,272,773,800.00 | | | 3,272,773,800.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 68 | ዘመናዊ የምድር ሚዛን መሰረተ ልማት ግንባታና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት | | 10,200,000,000.00 | | | 10,200,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 69 | የፍትሐብሄር ጉዳዮችና ተያያዥ የክትትል ስራዎች በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ | | 12,000,000.00 | | | 12,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 70 | የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ስራን በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ | | 12,000,000.00 | | | 12,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |

| የፕሮግራም ዝርዝር | ተራ ቁጥር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2016 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር) | የ2016 - 2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ዒላማዎች (በብር) | | | ድምር (2016-2018) | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ(በብር) | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌዴራል በጀት | የፌዴራል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳታ | ብድር(የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | | ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | | | | |
| | 71 | የሰው ሰራሽ አስተውሎትን መሰረት ያደረገ ቻትቦት፣የጉምሩክ አስተላላፊዎች እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ፕሮጀክት | | 10,000,000.00 | | | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 72 | የሰው ሰራሽ አስተውሎትን መሰረት ያደረገ የመንገደኞች ስጋት ስራ አመራር ፕሮጀክት | | 10,000,000.00 | | | 10,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 73 | ዘመናዊ የጉምሩክ ድንበር አስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት ፕሮጀክት | | 600,000,000.00 | | | 600,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 74 | የጉምሩክ ላብራቶሪ ማቋቋም፣ | | 1,500,000,000.00 | | | 1,500,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| | 75 | ከአዋሳኝ ሀገሮች ጋር የአንድ አለቅ ፕሮጀክቶችን /One Stop Border Post / ማጠናቀቅ*፣ | | 450,000,000.00 | | | 450,000,000.00 | | | | የፌዴራል በጀት | | | | | |
| ጠቅላላ ድምር | | | 3,220,825,102.90 | 29,616,452,883.99 | 17,678,987,040.42 | 15,496,631,027.36 | 63,423,842,176.86 | 17,370,555,580.96 | | | | | | | | |

# 6 ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች

የመካከለኛ ዘመን ዕቅዱን ለመፈጸም በሚደረገው እንቅስቃሴ የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ስጋቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከተለዩት ስጋቶች ውስጥ ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የህቡእ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የታክስ ህግ ተገዥነት ባህል ማነስ፣ ዝቅተኛ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የሰው ሀይል ፍልሰት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን ስጋቶችና ስጋቶቹን ለመቀነስ ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡ ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች**

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| **የዓለም ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ተለዋዋጭነት** | • የዓለም የፖለቲካ ሚዛን እና የኢኮኖሚ ሁኔታ መለዋወጥ (ለምሳሌ፡ የምዕራባውያን እና ምስራቃውያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፉክክር፣ የዩክሬን ጦርነት) በሀገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚንጸባረቅ በመሆኑ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፣ | • በዓለም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተለዋዋጭነት ምክንያት በታክስ አስተዳደሩ ላይ የሚከሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣ |
| **የህቡዕ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ** | • በህጋዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይታቀፉ በታክስ ማጭበርበር፣ ኮንትሮባንድ፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ ህገወጥ ደረሰኝ እና በመሳሰሉት ተግባራት ላይ በመሳተፍ በመንግስት ገቢ፣ በህጋዊ ንግድ እና በሀገር ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ህቡዕ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው ወደፊትም ችግሩ ሊቀጥል የሚችል መሆኑ፣ | • ህቡዕ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ መተግበር፣ <br>• በጥሬ ገንዘብ ላይ የተመሰረተውን የንግድ ግብይት በባንክ ስርዓትን እንዲተካ ማድረግ፣ <br>• በዋና ዋና የህቡዕ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ላይ የማያዳግም ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ፣ |
| **የህግ ተገዥነት ባህል አነስተኛ መሆኑ፣** | • ከግብይት ዋጋ በታችና በላይ ማቅረብ፣ ዋጋ ማሸጋገር፣ በመንግስት የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻዎችን አላግባብ መጠቀም፣ ያልተገባ ተመላሽ መጠየቅ፣ ገቢን በወቅቱ አለማሳወቅና አለመክፈል፣ አላግባብ ባዶ፣ ኪሳራና ተመላሽ ማሳወቅ ሊያጋጥም የሚችል መሆኑ፣ | • የህግ ተገዥነት ማሻሻያ ስትራቴጂ (Compliance Improvement Strategy) ቀርጾ መተግበር፣ <br>• የተቋሙን የህግ ማስከበር አቅም ማጠናከር፣ <br>• ህገወጥነትን በቅንጅት መከላከል፣ |
| **የቅንጅታዊ አሰራር ጉድለት** | • ከሀገር ውስጥና ከውጪ አጋር አካላት ጋር የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራር በሚጠበቀውና ውጤት ሊያስገኝ በሚችል ደረጃ ተግባራዊ | • በህግ ማዕቀፍ የሚደገፍና ተጠያቂነትን የሚያከትል ጠንካራ የቅንጅት ስትራቴጂ ቀርጾ |

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| | ሊደረግ አለመቻሉ፣ | መተግበር፣ |
| **የውጭ ምንዛሪ እጥረት** | • ሀገሪቱ ከውጭ ለምታስመጣቸው ዕቃዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲያጋጥማት መቆየቱ፣ ለወደፊቱም እጥረቱ ሊቀጥል የሚችልበት ዕድል ሰፊ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፣ | • ኤክስፖርትን መደገፍ፣<br>• ካለ ውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ሊገቡ የሚችሉበትን አማራጭ ሥርዓት መዘርጋት፣<br>• የፋይናንስ ገበያው ለውጭ ባንኮች ክፍት ማድረግ፣ |
| **የሰው ሀይል ፍልሰት** | • የዋጋ ግሽበት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተሻለ ገቢ ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ልምድና ሙያዊ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ፍልሰት መኖሩ፣ | • የኑሮ ደረጃውን ከግንዛቤ ያስገባ የሰራተኛ ማቆያ ሥርዓት (Retention Strategy) መዘርጋት፣ |

# 7 የክትትልና ግምገማ አሠራርና ሥርዓት

የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዱ በተቀላጠፈ እና ውጤታማ በሆነ መልክ ለማሳካት የተቀረጹ ፕሮጀክቶችና እንቬትሮች አፈጻጸም አንጻር በጥራት፣ በጊዜ እና በተያዘላቸው በጀት እየተፈጸመ መሆኑን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ፣ ግምገማ እና ግብረ መልስ እየሠጡ የልማትና የኢንቨስትምነት ዕቅዱ በተያዘው አግባብ እንዲሄድ ማድረግ ይገባል፡፡ የልማት ዕቅድ እና የኢንቨስትመንት ፕላን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዋና ዓላማ ዕቅዱ በተሟላ መልኩ በመከታተል በውጤታማነት እንዲተገበር ማስቻል ነው፡፡ የሚደረገው ክትትልና ግምገማ፣ በአፈጻጸም ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን በፍጥነት በመለየት አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ በመውሰድ ለውጤትና ስኬት የማብቃት ድጋፍ በመስጠት ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

ከዚህም በላይ በትግበራ ሂደት ውስጥ የሚታዩ የተሻለ አፈጻጸም በስኬት እና ከክፍተቶችም ጭምር ከተሞክሮ በመማማር (Learning by doing) ለበለጠ የመፈጸምና የማስፈጸም ብቃት ለመገንባት የሚያግዝ ሥርዓት ሆኖ ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም፣ በዕቅዱ የተያዙ ዒላማዎችና ዋና ዋና ተግባሮች በተጨባጭ ተፈትሸው በአንጻራዊነት የሚከለሱበትና የሚስተካከሉበት ምቹ ሁነታ ከመፍጠሩም ባሻገር በአፈጻጸም ሥርዓት ዙሪያ ግልጽነትን በማስፋት ተጠያቂነትን ለማስፈን ያለመ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም፣ የክትትልና ግምገማ አሠራር፣ ለክትትልና ግምገማው የሚያስፈልግ አደረጃጀትና ሰው ሀይል፣ ክትትልና ግምገማውን በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂና አሠራር ሥርዓት መደፍ ያስፈልጋል፡፡

## 7.1 የክትትል ሥርዓት

የልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ አስፈጻሚ አካላት ሁሉ በተዋረድ በተዘጋጀው ዕቅድ መሠረት አፈጻጸማቸውን የመከታተልና የመገምገም ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ክትትል የሚከናወንባቸው ዜዴዎች፣ በስልክ፣ በአካል ግንኙነት እና ለዚሁ ዓላማ በተቀረፀ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሠረት በሚቀርብ የጽሁፍ ሪፖርት መሥረት ይሆናል፡፡ ከየዳይሬክቶሬቶች እና ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቀርበው ወራዊና የሩብ ዓመት ሪፖርቶች አንጻር በከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን በመለየት እንደየአፈጻጸማቸው ደረጃ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት፣ በዝቅተኛ አፈጻጸም የታዩትን ለዚሁ ዓላማ በሚቋቋመው የሱፐርቭዥን ቡድን በመስክ የሥራ ጉብኝት በማድረግ የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀትም ጭምር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

